# “የአእላፋት ዝማሬ”

**በርናባስ ሽፈራው**

† † †

ሁለተኛው የአእላፋት ዝማሬ ባለፈው ዓመት በልደት ዋዜማ ተካሔደ ። በአዘጋጆቹ እና በተሳታፊዎቹ ዘንድ ይህ ሁለተኛው ዙር ከመጀመሪያው ዙር በላይ ያማረ እና የሠመረ ሆኖ ተቆጥሯል ። በጠቅላላው ከምእመናን በኩል በተሳትፎም ሆነ በማኅበራዊ ሚዲያ ያገኘው ተቀባይነት ሌሎች ሁነቶች ሲሆኑ እንደምናየው በጅምር የሚቀር ሳይሆን እንደ ባህል የመተከል ዕድሉ ሰፊ መሆኑን ያመላክታል ። እንዲያውም በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ብቻ ሳይወሰን ወደ ሌሎች ቦታዎችም እንዲሰፋ የሕዝብ ጥያቄ እና በአዘጋጆቹም በኩል እቅድ መኖሩ ይታወቃል ። ስለዚህ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ልክ እንደ ጥምቀት ሁሉ በሁሉም ዋና ዋና ከተሞች ውስጥ (የአዘጋጆቹ አቅም በፈቀደው ልክ) የአእላፋት ዝማሬ የልደት በዓል መለያ ሆኖ እንዲካሔድ መጠበቅ እንችላለን ።

ይህ ነገር በብዙዎች ዘንድ ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ጥቅም የሚሰጥ ሆኖ ይታያል ። በእነርሱ ዐይን ይህ ሁነት ቤተ ክርስቲያን በብዙዎች ዘንድ እንድትታወቅ ያደርጋል ። ብዙዎች በዓሉን አስመልክተው ከሚሔዱባቸው የማይገቡ ዓውዶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመለሱ ከማድረጉ ባሻገር ፥ በቤተ ክርስቲያን ሱታፌ ያላቸውንም በሚስብ እና በሚገባቸው መልኩ ቤተ ክርስቲያንን የበለጠ እንዲያውቋት ያስችላቸዋል ። ስለዚህም የሌሉትን በመጥራት ፥ ያሉትንም በማጽናት ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን እንድትዋጅ የሚያስችላት መሣሪያ ነው ፤ ከእርሷ ዘንድ ወደ ክሕደት እና ወደ ኑፋቄ የፈለሰውን ፥ ወይም በስም ክርስቲያን ሆኖ እና ማዕተብ አስሮ ሳለ በምድራዊ ተድላ ባሕር የሰጠመውን ወጣት ወደ ራሷ የምትስብበት መረብ ነው ።

ነገር ግን ከኖረው የቤተ ክርስቲያን ትውፊትና አስተምህሮ አንጻር ከመረመርነው ፥ ይህ ሁነት እና ሁነቱን ያፈራው ባህል ለቤተ ክርስቲያን ትልቅ አደጋ መሆናቸውን እንመለከታለን ። ተፈጥሮውንና ቅኝቱንም ከክርስትና የተቃረኑ ሆነው እናገኛቸዋለን ። በሚከተሉት ገጾች ውስጥ ይህ እንዴት እንደሆነ ለማብራራት እሞክራለሁ ።

※ ※ ※

ስለ አእላፋት ዝማሬ በመጀመሪያ መጠየቅ የሚገባው ጥያቄ ‘ለምን’ የሚል ነው ። ‘የአእላፋት ዝማሬ’ ለምን መዘጋጀት አስፈለገው ? ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ልደትን የምታከብርበት ሥርዓታዊ መንገድ እንዳላት ይታወቃል ። ታዲያ ልደትን ለማክበር ከዚህ ሥርዓታዊ መንገድ የተነጠለ ሌላ አከባበር ያስፈለገው ለምድነው ? ልደት በሁሉም ደብሮች የሚከበር በዓል እንደመሆኑ ጥሪው ለምን በየደብሩ ወዳለው አከባበር አልሆነም ? ኑ ማኅሌት እንቁም ፥ ከዚያም እናስቀድስ የሚል ለምን አልሆነም ? ቤተ ክርስቲያን ልደትን ለማክበር የደገሰችው ድግስ ይህ ሆኖ ሳለ ፥ ለምን ከዚህ የተለየ ሁነት መዘጋጀት አስፈለገው ?

የአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆች በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ልደትን ለማክበር በየደብሩ ከሚከናወኑት ግብሮች በተለየ ይህን ሁነት ለምን ማዘጋጀት እንዳስፈለገ ያስረዱት ልደትን በማይገባ መልኩ ፥ ማለትም በዘፈን፣ ኮንሰርቶችና በጭፈራ ቦታዎች ፥ የሚያሳልፉ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን ከእነዚያ ቦታዎች አስቀርቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማምጣት የሚደረግ ነው በማለት ነበር ። ከሁለተኛው የአእላፋት ዝማሬ አስቀድሞ በሰጡት መግለጫም ይህኑ አረጋግጠውልናል ።

ከዚህ መልሳቸው የምንረዳው ፥ በቤተ ክርስቲያን ያለው ሥርዓታዊ የበዓል አከባበር ፥ ቢያንስ እነርሱ የጠቀሷቸውን ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመጥራት በቂ ነው ብለው እንደማያስቡ ነው ። ሥርዓተ አምልኮአዊ የሆነው የበዓል አከባበር ምሉዕ ነው ብለው ቢያስቡ ሌላ አማራጭ መፍጠር ባላስፈለጋቸው ነበር ።

አንድ ሰው ምን ችግር ሊፈታ እንዳሰበ ከመፍትሔው ይታወቃል ። ኢጃትም የአእላፋት ዝማሬን በማዘጋጀቱ ሥርዓታዊ በሆነው የበዓል አከባበር ሊሸፈን የማይችል አንዳች ጉዳይ እንዳለ መናገሩ ነው ። የሁነቱ አዘጋጆች ይህን አፍ አውጥተው አልተናገሩም ። ይህን የማያደርጉት ምናልባት አሁን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ተዋሥኦ በኦርቶዶክሳውያን መካከል ምንም ዓይነት መተቻቸት

ሊኖር አይገባም በሚል መርሕ የሚመራ ስለሆነ ፥ ይህን ያልተጻፈ ሕግ ሳለመሻር ይሆናል ። ምናልባት ደግሞ ሐሳቡ እስካሁን ከነበራቸው ተሞክሮ ሳያውቁት በውስጣቸው ያደረ እንጂ እየታወቃቸው በአእምሮአቸው ያመላለሱት ስላልሆነ ሊሆንም ይችላል ። የአእላፋት ዝማሬን ሲጀምሩም ሥርዓታዊ ከሆነው አምልኮ ጋር ያለው ተቃርኖ አልታሰባቸውም ይሆናል ። ምክንያቱም ሥርዓታዊ ከሆነው አምልኮ ጋር የሚገዳደሩ ሁነቶችን የማዘጋጀቱ ነገር በአእላፋት ዝማሬ የተጀመረ አይደለም ። ቢያንስ ባለፉት ሠላሳ ወይም አርባ አመታት የነበረ እና በአሁኑ ወቅት በእጅጉ ዳብሮ የሚገኝ "ትውፊት" ነው ። ስለዚህ የኢጃት ሰዎችም በዚህ "ትውፊት" ውስጥ እንደመኖራቸው የአእላፋት ዝማሬን ሲያዘጋጁ የሚያውቁትን አገልግሎት የማዳበር እና የማስፋት እንጂ ከኖረው ትውፊት የመጣላት እና የመተቸት አድርገው ላያስቡት ይችላሉ ።

ሥርዓታዊ የሆነው አምልኮ በቂ አይደለም ተብሎ ሊታሰብ የቻለበት ምክንያት ምን እንደሆነ ይገባኛል ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ሥርዓታዊ የበዓል አከባበር ሁሉም ምእመን ሊረዳውና ሊሳተፍበት የሚችል ቢሆን ኖሮ ኢጃት የአእላፋት ዝማሬን አያዘጋጅም ነበር ። ቢያዘጋጅም ሥርዓታዊውን አምልኮ የተረዳ እና ያጣጣመ ምእመን ወደ አእላፋት ዝማሬ ሊሔድ የሚችልበት ዕድል አይኖርም ነበር ። ነገር ግን በዓላትን በቤተ ክርስቲያን አሳልፎ የሚያውቅ ሰው እንደሚያውቀው በበዓል የሚቆመውን ማኅሌት አብዛኛው ምእመን መረዳት አይችልም ። ስለዚህ ሌሊቱን ተቀምጦ በማንቀላፋት ወይም ሌላ ነገር በማሰብ ለማሳለፍ ይገደዳል ።

በበዓል ብቻ ሳይሆን በአዘቦትም ቢሆን እንደኔ ያለው ምእመን የማይሰማውና የማይረዳው ነገር ይበዛል ። ለምሳሌ ኪዳን ለማድረስ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣ ሰው የጸሎቱን ይዘት አያውቀውም ። ቢያንስ ማኅሌቱ በግዕዝ ተደርሶ ከዜማ ጋር የተሰፋ ስለሆነ ማኅሌቱን የሚቆሙት ደባትር በግዕዝ ከማዜም ውጭ አማራጭ የላቸውም ። የኪዳኑን ወይም የቅዳሴውን ጸሎት ግን ምእመኑ እንዲሰማው አድርጎ ማንበብ ይቻላል ። ነገር ግን ሕዝቡ ጸሎቱን መስማቱ አስፈላጊ ነው ተብሎ አይታሰብም ።

ይህ ዛሬ የመጣ ችግር አይደለም ። በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ለረዥም ዘመናት የኖረ ነው ። ብዙ ዋጋ ያስከፈለንም ጉድለት ነው ። 'ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?' የሚለው ሰፊ ታሪካዊ መልስ የሚፈልግ ጥያቄ ነው ። በአጭሩ ግን ግዕዝ በመጀመሪያ የቤተ ክርስቲያን ቋንቋ የሆነው የሕዝቡ ቋንቋ ስለነበረ ነው ። ነገር ግን በጊዜ ሒደት ግዕዝ የሕዝብ ቋንቋ መሆኑን ሲያቆም ፥ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን መጻሕፍቱ ሁሉ በግዕዝ መጻፋቸው ፣ መነበባቸውና እና መዜማቸው ቀጠለ ። የሕዝቡ ቋንቋ ከግዕዝ እየራቀ በመጣ ቁጥርም ሕዝቡ ሥርዓተ አምልኮውን ለመረዳት ያለው ችሎታም በዚያው መጠን እየቀነሰ መጣ ። ይህ መሆን አልነበረበትም[1] ።

አባቶቻችን ይህን ችግር ለመፍታት የሚቸገሩባቸው ብዙ ምክንያቶች ነበሩ ይሆናል ። ነገር ግን ለማድረግ ፈልጎ ካለመቻል ባሻገር (ምናልባትም በጊዜ ሂደት) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን አገልግሎቶች ይዘት ምእመኑ መረዳቱ አስፈላጊ አይደለም የሚል ድምዳሜ ተፈጠረ ። ኪዳን ፥ ቅዳሴ ፥ ማኅሌት እና ሌሎችም አገልግሎቶች ሕዝቡ ቆሞ ሊመለከታቸው ፥ ካህናትና ደባትር ብቻ ሊረዷቸው የተፈጠሩ ተደርገው እስከ መታሰብ ደረሱ ። ብላታ መርስዔ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ በግለ ታሪካቸው ውስጥ የመዘገቡት አንድ ታሪክ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ይሆነኛል ።

> "አባ ኪዳነ ማርያም (የሐዲስ ፣ የፍትሐ ነገሥት እና የቅዳሴ መምህር) የንግግር ተሰጥዎ ያላቸው ሰባኪ ስለሆኑ በሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት በቅዳሴ ላይ እየሰበኩ ለካህናቱና ለሕዝቡ ልዩ ልዩ ሥርዓትን አስለመዱ ። ይኸውም የሚከተለው ነው ።
>
> አንደኛ ፣ ፍትሐት ዘወልድና በእንተ ቅድሳት ፣ ጸሎተ ንስሐም በሚደገምበት ጊዜ ግንባርን መሬት ደፍቶ መንበርከክ እንደሚገባ በቅዳሴው ላይ ተጽፎ የቆየ ሥርዓት ሲሆን በከተማችን ተዘንግቶ ይኖር ነበር ። አባ ኪዳነ ማርያም ግን ይህን ሥርዓት ለማስለመድ እየሰበኩና ምሳሌነታቸውን እያሳዩ ሁሉም እንዲንበረከክ አደረጉት ።
>
> ሁለተኛ ፣ በቅዳሴው ላይ የሚነበበውን ጳውሎስና ሐዋርያ ፣ ግብረ ሐዋርያ ፣ ወንጌል ፥ በግዕዝ ብቻ እንጂ በአማርኛ ማንበብ ገና አልተጀመረም ነበር ። እሳቸው ግን ከግዕዝ ቀጥሎ በአማርኛም እንዲነበብ ማድረግን በብዙ ድካም አስለመዱ ። በዚህ ጊዜ ከካህናት

[1] በጎንደር ዘመን የመጻሕፍት የአንድምታ ትርጓሜ በአማርኛ ተዘጋጅቶ ነበር ። ነገር ግን ይህ ጅምር በሥርዓተ አምልኮውና በሌሎች ዘርፎች አልቀጠለም ።

አንዳንዶቹ በአማርኛ ማንበብ የፕሮቴስታንት ባሕል ነው እያሉ መንቀፍ ጀምረው ነበር ። ሆኖም ውሎ አድሮ ስለተለመደ በሁሉም ዘንድ የሚደረግ ሆኗል ።

ሦስተኛ ፣ ዲያቆን የበዓሉን ምስባክ በግዕዝ ከሰበከ በኋላ በአማርኛ እየተረጎሙ ለሕዝብ ያሰሙ ነበር ። ይህን ሥርዓት ብቻ ሌሎች ሳይከተሉላቸው ቀርተዋል ።

አራተኛ ፣ በቅዳሴ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከቆሙት ካህናትና መኳንንት አብዛኞቹ በቃልም በመጽሐፍም የግል ጸሎት ሲያደርሱ ይታዩ ነበር ፤ አባ ኪዳነ ማርያም ግን ተሰጥዎ ከመቀበል ወይም ቅዳሴውን ከማዳመጥ በስተቀር በቅዳሴ ላይ የግል ጸሎት አይገባም ብለው በስብከታቸው ተከላከሉ ።

. . . አባ ኪዳነ ማርያም በአበው መጽሐፍ ከታዘዘው ውጭ በልማድ ገብቶ የቆየውን አሮጌውን ሥርዓት ለማሻሻልና በመጽሐፍ የታዘዘውን ለመተካት በእውነት ይደክሙ ነበር ። ደብተሮች በከበሮ የሚያደምቁትንም ሽብሸባ ከቁም ነገር ስለማይመለከቱት አንዳንድ ሰው የፕሮቴስታንት ባሕል ይዘዋል እያለ ያማቸው ነበር ። እሳቸው ግን አልነበሩም ።"[2]

እንዲህ ያለው መረዳት እንደ ባሕል ሆኖ ተተክሎብን ቆይቷል ። ነገር ግን ምንም ያህል ቢቆይ ስህተት ስለሆነ መታረም አለበት ። በምእመኑ እና በሥርዓተ አምልኮው መካከል ድልድይ መሥራት ያስፈልጋል ። ይህ ደግሞ የተጀመረ ነገር ነው ። በተለያዩ ጊዜያት ቅዱሳት መጻሕፍትም ሆኑ የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍት ከግዕዝ ወደ አማርኛ እና ወደሌሎችም ቋንቋዎች ተመልሰዋል ፥ እየተመለሱም ነው ። እንደሚገባውም ባይሆን ሥራ ላይ ይውላሉ ። ይህ መቀጠል ያለበት ሒደት ነው ። መጻሕፍቱን ከመተርጎም ባሻገር ደግሞ እንደሚገባቸው በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ ያስፈልጋል ። ምክንያቱም ከላይ እንዳነሣሁት ዛሬም ቢሆን በአብዛኛው አጥቢያ ምእመኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔዶ ዋናውን የአገልግሎቱን ክፍል ሳይሰማ እየተመለሰ በመሆኑ ነው ።

የአእላፋት ዝማሬ ግን እንዲህ ያለውን ድልድይ ከመገንባት ይልቅ በምእመኑ እና በሥርዓተ አምልኮው መካከል ያለውን ርቀት የሚያነብር እና የሚያሰፋ ሁነት ነው ። ምክንያቱም የአእላፋት ዝማሬ የወሰደው ተልእኮ በሥርዓተ አምልኮው ውስጥ ያለው የበዓል አከባበር ካለው ተልእኮ ጋር ተመሳሳይ ነው ። በጌታ ልደት ከተደሰቱት መላእክትና እረኞች ጋር ፣ ከሰብአ ሰገል ጋር መደሰትና መዘመር የማኅሌቱና የቅዳሴው ተልእኮ ነው ። አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ተመሳሳይ ተልእኮ መውሰዱ በሁለት መንገድ ነው ሊተረጎም የሚችለው ። ወይ ከመጀመሪያው ጋር አብሮ ሊሠራ ነው ። ያ ካልሆነ ግን የመጀመሪያውን ሰው ሊተካው ነው ። ስለዚህ የአእላፋት ዝማሬም ይህን ተልእኮ ይዞ ሲነሣ ሊያደርግ የሚችለው ሁለት ነገር ነው ። ወይ የሥርዓተ አምልኮው ተጨማሪ አካል ይሆናል ። አሊያም ሥርዓተ አምልኮውን በሙሉ ወይም በከፊል ይተካል ።

ሥርዓተ አምልኮው ላይ መጨመርና ማዳበር የማይቻልና የማይሆን ነገር ሆኖ አይደለም ። አባቶቻችን ሲያደርጉት የኖሩት ፥ አሁንም በተገቢው መንገድ ሊደረግ የሚችል እና የሚገባም ነው ። የአእላፋት ዝማሬ ግን ከሥርዓተ አምልኮው የተነጠለ እንጂ የሥርዓተ አምልኮውን አካሔድ ተከትሎ የተጨመረ ነገር አይደለም ። ስለዚህ ሊኖረው የሚችለው ሚና ሥርዓተ አምልኮውን በከፊል ወይም በሙሉ መተካት ነው ። እየሆነ ያለውም ይኸው ነው ።

※ ※ ※

ይህ ሥርዓተ አምልኮውን ከማዕከላዊ እና ሁለተናዊ ሚናው የመግፋት ሒደት በአእላፋት ዝማሬ የተጀመረ አይደለም ። ሥርዓታዊ የሆነውን አምልኮ የሚገዳደሩ ሌሎች ሥርዓታዊ ያልሆኑ የአምልኮ መንገዶች ከተፈጠሩ ቆይተዋል ። ይህን መንገድ የጀመሩት አሁን በኦርቶዶክሳውያን ሕይወት ውስጥ የጎላ ሚና ይዘው የሚታዩት ዘመናዊ መዝሙሮች እና ስብከቶች ናቸው ።

እነዚህ መዝሙሮችና ስብከቶች ወደመናር የመጡት እና የዳበሩት ከምዕራባዊው ሥልጣኔ መምጣት በኋላ ነው ። ከምዕራባዊው ሥልጣኔ ወደ ሀገራችን መግባት ጋር ተያይዞ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ዐዳዲስ ዕድሎችም ፥ ብዙ ዐዳዲስ ፈተናዎችም ገጥመዋታል ። እነዚህን ዕድሎች ለመጠቀም እና ፈተናዎቹን ደግሞ ለመቋቋም የተሠሩ ሥራዎች አሉ ።

---

[2] መርስዔ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ ፣ *ትዝታዬ* (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ) ፣ ገጽ 68

የሁኔታዎችን መለዋወጥ ተከትሎ ዐዳዲስ ሥራዎች መሠራታቸው አስፈላጊ ነበር ። የእነዚህ ዐዳዲስ ሥራዎች ሚና ግን በዋናነት የኖረውን አስተምህሮና ትውፊት ዘመኑ በፈቀዳቸው እና በጠየቃቸው መንገዶች የማርዘም እንጂ ከዚያ የተነጠለ ዐዲስ ትውፊት መፍጠር ሊሆን የማይገባ መሆኑ የሚያስማማን ይመስለኛል ። ይህን ሚና በሚገባ የተወጡ ሥራዎች ነበሩ ። ለምሳሌ ከላይ እንዳልሁት ዘመናዊውን የኅትመት ቴክኖሎጂ በመጠቀም ብዙ መጻሕፍትን ሕዝቡ መስማትና ማንበብ ወደሚችላቸው ቋንቋዎች የመተርጎም ሥራ በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ነው ።

ነገር ግን የትርጉም ሥራዎቹም በሚገባ ሥፋት አልተሠሩም ። የተሠሩትም በሚገባ ሥራ ላይ አልዋሉም ። የቀደመው ልማድ ሰፍኖ ቀጠለ ። ስለዚህም በሥርዓተ አምልኮው እና በምእመናን መካከል የነበረው ርቀት ጸንቶ ቀጠለ ። ይህ ክፍተት ቀድሞም የነበረ ቢሆንም ፥ ምዕራባዊው ሥልጣኔ ከመጣ በኋላ ግን ጉልህ ሆኖ ታየ ። የዘመናዊው ትምህርት ስሑት መነሻዎች እና የምዕራቡ ዓለም ኑፋቄዎች በስፋት ወደሀገራችን ሲተዋወቁ ምእመኑ እነዚህን የሚመክትበት ነገረ ሃይማኖታዊ ትጥቅ አልነበረውም ። ሥርዓተ አምልኮውና ቅዱሳት መጻሕፍት ነበሩ ትጥቅ ሊሆኑት የሚገባቸው ። ነገር ግን ከላይ እንዳየነው ምእመኑ ከእነዚህ የክርስትናውን ይዘት የሚያስረዱ ምንጮች ተገልሎ በመኖሩ ምክንያት ከምዕራብ የመጣው ባሕል እና ኑፋቄ ፈጽሞ በተጋለጠ ሁኔታ አገኙት ። ይህን ክፍተት ለመሙላት ልዩ ልዩ ሙከራዎች ተደርገዋል ። ሰንበት ትምህርት ቤቶች ፣ ቅድስት ሥላሴ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ፣ ሃይማኖተ አበው የሚባለው ማኅበር ወዘተርፈ የዚህ ጥረት አካላት ነበሩ ። ዘመናውያኑ መዝሙሮች እና ስብከቶችም እንዲሁ ።

የመዝሙሮቹና የስብከቶቹ ሚና አብዛኛው ሕዝብ የሚረዳው ይዘት መፍጠር ነው ። ሰዉ ቤተ ክርስቲያን ሔዶ የሚከናወነውን ነገር መረዳት አለበት የሚለው መነሻ ተገቢ ነው ። ነገር ግን ይህን ክፍተት ለመሙላት የተሔደበት መንገድ ጥፋት ነበር ። ምክንያቱም ይህ ሚና የሥርዓተ አምልኮው ነው ። መዝሙሮችና ስብከቶች ወደ ዓውደ ምሕረት ሲወጡ ሥርዓተ አምልኮውን በከፊል የመተካት ሚና ነው የወሰዱት ። ምክንያቱም ይህ ሒደት ከተጀመረ በኋላ ምእመኑ ሥርዓተ አምልኮውን አለመረዳቱ እንዳለ ሲቀጥል ፥ መዝሙሮችና ስብከቶች ግን ለአብዛኛው ምእመን በቤተ ክርስቲያን ሱታፌ የሚያደርግባቸው ዐበይት መንገዶች ሆነው ብቅ አሉ ።

ለዚህ ብዙ ማስረጃ አያሻኝም ። ዛሬ አንድ ሰው እሑድ ጠዋት ተነሥቶ ወደ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ሊያረጋግጠው የሚችለው ነገር ነው ። ቅዳሴውን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ለመሳተፍ ከፈለገ በብዙዎቹ ደብሮች ከ11 ሰዓት በፊት መድረስ ይኖርበታል ። ጥረቱ ምእመናን ሳይደርሱ ቅዳሴው እንዲፈጸም ነው የሚመስለው ። ቅዳሴው ሲከናወንም ደግሞ ሁሉም ሰው መከታተል እንዲችል አሰምቶ ማንበብና ሁሉንም ነገር በእርጋታ እና በመጠባበቅ ማከናወን በተገባ ነበር ። ነገር ግን በአብዛኛው ቦታ እና ጊዜ በብዙ ጥድፊያ እና ችኮላ ነው የሚቀደሰው ።

አብዛኛው ምእመን ሞልቶለት በሚደርስበት ጊዜ ቅዳሴው ወደ ማለቁ ነው ። ምእመኑ በዋናነት የሚካፈለው ከቅዳሴ በኋላ በዓውደ ምሕረቱ ላይ የሚቀርበውን ስብከትና መዝሙር ነው ። ማኅሰቢያውም ምእመናን ይህን የዓውደ ምሕረት ጉባኤ ጨርሰው ሳይታደሙ እንዳይሔዱ ነው ። ካህናቱም ቅዳሴው ቢያበቃም ሕዝቡን የማያሰናብቱት ለዚሁ ሲባል ነው ።

በዚህ ውስጥ የምናየው ሥርዓተ አምልኮው የትምህርትና የመረዳት ሳይሆን የድጋም ዓውድ ተደርጎ እንደሚታይ ነው ። ይልቁንም ከቅዳሴ በኋላ ያለውን መዝሙርና ስብከት ነው ሕዝቡ እንዲረዳው የሚታሰበው ። ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ አገልግሎቶች በሠርክ ጉባኤ ፣ በልዩ ጉባኤ ፣ በአዳራሽ ጉባኤ ፣ በገቢ ማሰባሰቢያ ፣ በጉዞ እና በሌሎችም ልዩ ልዩ ዓውዶች በመደበኛነት ስለሚካሔዱ ብዙ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ስለሚካሔደው አገልግሎት ምንም ዕውቀት ሳይኖራቸው የክርስትናቸው መገለጫ ከመዝሙርና ከስብከት እነዚህን በመሳሰሉ ዓውዶች አማካይነት ያላቸው ሱታፌ ብቻ እንዲሆን ሆኗል ። ቤተ ክርስቲያንን በመወከል በቀዳሚነት በምናባቸው ውስጥ የሚከሰቱትም ጥቂት ሰባክያን እና ዘማርያን ናቸው ። እንደምንኮራበት ሳይሆን የቅዱስ ያሬድ ነገረ ሃይማኖት በተቃራኒው ከምእመናን የተሰወረ ነው ። የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ይዘታቸው ቀርቶ ብዛታቸው እና አርእስቱ እንኳን ለአብዛኛው ምእመናን የታወቁ አይደሉም ። የመጽሐፈ ቅዳሴ ይዘትም እንዲሁ ። በተቃራኒው የገነኑት ሰባክያን እና ዘማርያን ስብከቶችና መዝሙሮች ግን ቃል በቃል የታወቁ ናቸው ። ታዲያ ስብከትና መዝሙር የሥርዓተ አምልኮውን ሚና አልነጠቁም ብሎ ሊከራከር የሚችለው ማነው ?

እነዚህ የመዝሙርና የስብከት ዓውዶች ሥርዓታዊ ከሆነው ሥርዓተ አምልኮ ጋር ከመገዳደራቸው

በተጨማሪ የይዘታቸው ነገርም በእጅጉ አጠያያቂ ነው ። የአእላፋት ዝማሬ በአዘጋጆቹ የተመረጡ ዘመናይ ዝማሬዎች ተከታትለው በኅብረት የሚዘመሩበት ሁነት ነው ። እነዚህ ዝማሬዎች ሥርዓታዊ በሆነው አምልኮ ውስጥ ከምናገኛቸው ዝማሬዎች ጋር ልዩነት ያላቸው መሆኑ የታወቀ ነው ። ቢያንስ በዜማ እና በቋንቋ በኩል ያላቸውን ልዩነት ማንም ማስተዋል የሚችለው ነው ። ነገር ግን ሁለቱም አንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደመገኘታቸው የጎላ የይዘት (የነገረ ሃይማኖት) ልዩነት ሊኖራቸው አይገባም ነበር ። እውነታው ግን በዚህ ረገድ በሁለቱ መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩ ነው ።

ነገሩ በሰፊው መጠናት ያለበት ቢሆንም የሁለቱንም ይዘት በተወሰነ ደረጃ ላወቀ ሰው ይህ ልዩነት ልክ በዜማ በኩል እንዳላቸው ልዩነት በጉልህ የሚታይ ነው ። በቅዳሴ ፥ በዜማ እና በአቋቋም ቤቶች ውስጥ የሚገኙትን ድርሰቶች ይዘት በአሁኑ ወቅት ሰፊ ተደማጭነት ካላቸው ዘመናውያን ዝማሬዎች ይዘት ጋር ማነጻጸር ይህን ለመረዳት በቂ ነው ።

ዜማን በተመለከተ በሁለቱ መካከል የሚታየው መሠረታዊ ልዩነት ፥ ጥንታውያን እና ሥርዓታዊ የሆኑት ዝማሬዎች በየሚሰጡባቸው ቤቶች ውስጥ (ምንም እንኳን ልዩ ልዩ ይትበሃሎች ቢኖሩም) ዜማቸው የሚታወቅ ሥርዓት ፣ መለኪያና መሥፈሪያ ያለው ነው ። በየጊዜው ቢዳብሩም እንኳን ቀድሞ የተጣለውን መሠረት በመያዝ እዚያ ላይ የሚገነቡ ናቸው ። ዘመናውያን ዝማሬዎች በተቃራኒው (ከሚጠቀሙባቸው የዜማ መሣሪያዎች ባለፈ) የሚታወቅ መሥፈሪያ እና መለኪያ የላቸውም ። ይህ ነገር አንዳንዴ ውዝግብ ሲፈጥር ይታያል ። ብዙ ጊዜ ውዝግቡ የሚፈጠረው አንዳንድ መዝሙሮች ወይ የፕሮቴስታንት መዝሙር አሊያም የዘፈን የሚመስል ቃና በውስጣቸው ሲደመጥ ነው ።

ይኸው ችግር ግን ይዘታቸውንም በተመለከተ ሊነሣ ይችላል ። በሥርዓተ አምልኮ ውስጥ የምናገኛቸው ዝማሬዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት እና ከአባቶች አስተምህሮ የሚቀዳ ይዘት ነው ያላቸው ። ይህን ስል ቅዱሳት መጻሕፍት መጠቀሳቸውን ማለቴ አይደለም ። ይልቁንም ጥቅም ላይ የሚውሉበት መንገድ በኖረው የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ውስጥ ከሚተረጎሙበት እና ጥቅም ላይ ከሚውሉበት መንገድ ጋር የሠመረ ነው ማለቴ ነው ። ልዩ ልዩ በሆኑት አገልግሎቶች ውስጥ በአመዛኙ ያንኑ ነገረ ሃይማኖት ነው የምናገኘው ።

ዘመናውያኑ መዝሙሮች ግን በተቃራኒው ይዘታቸው በእጅጉ ዝርው ነው ፤ የሚቀዳው ከኖረው ትውፊት አይደለም ። ይልቁንም ይዘታቸውን በመወሰን ውስጥ ሁለት ነገሮች ጎልተው ይታዩኛል ። የመጀመሪያው ከፕሮቴስታንቶች ጋር የሚካሔዱት ዘመነኛ ክርክሮች ናቸው ። ዝማሬዎቹ በእነዚህ ክርክሮች ውስጥ ያሉትን ነጥቦች በዜማ የማስተጋባት ሚና ነው የሚታይባቸው ። የስኬታቸው መለኪያም በምእመኑ ዘንድ የሚኖራቸው ተቀባይነት ከመሆኑ የተነሣም ሰው መስማት የሚፈልገውን ነገር የመስበክ ጠባይዕ ኖሯቸዋል ። በዚህ ላይ ደግሞ በካሴትና በሲዲ ፣ አሁን ደግሞ በዩቲዩብ እና በሌሎች ማኅበራዊ ሚዲያዎች መሠራጨት እንደመቻላቸው እና ይህም ገንዘብ እንደማስገኘቱ ገበያ መር የሆነ አካሔድ በስፋት ይታይባቸዋል ።

በአንጻሩ አቋቋም ወይም ዜማ የተማረ አንድ ሊቅ ለሙያው ተጠያቂነት አለበት ። የሚያስተምረው የተቀበለውን ነው እንጂ ሰው መስማት የሚፈልገውን ሊሆን አይችልም ። ዐዲስ ድርሰት ቢደርስ እንኳን በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ ቦታ እንዲይዝ እንጂ ለእርሱ የሚያስገኝለት የተለየ ጥቅም አይኖርም ። ድርሰቱ ሥርዓታዊ ወደሆነው አምልኮ ይገባ ዘንድ ደግሞ ዜማውም ሆነ ነገረ ሃይማኖታዊ ይዘቱ ከኖረው ትውፊት ጋር የሚስማማ መሆን አለበት ። ስለዚህ ገበያን የመከተል ፈተና የለበትም ።

በእነዚህና ምናልባትም እኔ ልብ ባላልኳቸው ሌሎች ምክንያቶች ዘመናዊው የመዝሙር ‘ኢንዱስትሪ’ ከሥርዓታዊው ዝማሬ ጋር የማይነጻጸር እና አንዳንዴም የሚጣላ ይዘት ነው ‘የሚያመርተው’ ። ጥሩ ይዘት ያላቸው ዘመናዊ ዝማሬዎች የሉም ማለቴ አይደለም ። መኖራቸውን አውቃለሁ ። ነገር ግን አብዛኞዎቹ ጥልቀት የሌላቸው እና ለገበያ የተመረቱ ከመሆናቸው የተነሣ ጥቂቶቹን ጥሩ ሥራዎች በረሃ ላይ የበቀሉ አበቦች አድርጌ ነው የምመለከታቸው ።

(በዚህ ጽሑፍ ስለ ዘመናዊ ዝማሬ እና ስብከት ስጽፍ እና አሁን ያላቸውን ይዘትና የተሰጣቸውን ቦታ ስቃወም በጠቅላላው ስለ መዝሙር ፣ በጠቅላላውም ስለ ስብከት መናገሬ እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል ። ጥያቄው በቅድሚያ የይዘት ነው ። መዝሙሮችም ሆኑ ስብከቶች ከትክክለኛው ነገረ ሃይማኖትና በሥርዓተ አምልኮው ከሚገኘው መንፈስና ጥልቀት ሊርቁ አይገባም ። ይዘታቸው ከሥርዓተ አምልኮው ጋር ተመሳሳይ እስከሆነ ድረስ በሁለቱ መካከል አሁን እንደምናየው ያለ ውጥረት

እና መጓተት አይፈጠርም ። ሁለተኛው እና ዋናው ጥያቄ ደግሞ የቅድሚያ እና የዓውድ ነው ። ሥርዓተ አምልኮው ውስጥ የማይካተቱ ግን ሕዝባዊም ሆነ ግለሰባዊ ምንጭ ያላቸው መዝሙሮች መኖራቸው አይቀሬ ቢሆንም እና ባይጠላም ፥ ሥርዓተ አምልኮውን የመጋፋት ወይም የመተካት አዝማሚያ ግን ሊኖራቸው አይገባም ።

ስብከቶቹን በተመለከተ ደግሞ ቅኝታቸው ከተስተካከለ ፥ ማለትም ገበያ መር እና ብሽሽቃዊ ከመሆን ወጥቶ ፣ በሥርዓተ አምልኮው ውስጥ የምናገኘውን ጥልቅ ነገረ ሃይማኖት ገንዘብ ለማድረግ ከቻለ በሥርዓተ አምልኮው ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ ባሉ ዓውዶች ምእመናንን ይጠቅማል እንጂ የሚጎዳ ሊሆን አይችልም ። ቀድሞም ቢሆን ስብከት የሥርዓተ አምልኮው አንድ አካል ነው ። እንደ ጥንቱ ሥርዓት ቢሆን በቅዳሴው መካከል ወንጌል ከተነበበ በኋላ ካለ ጳጳሱ ፣ ከሌለም ሠራኢው ካህን የተነበቡትን ምንባባት እና የተሰበከውን ምስባክ አብራርቶ ለሕዝቡ ማስተማር ይገባዋል ። ከሥርዓተ አምልኮው ውጪም ቢሆን በተገኘው ዓውድ ትምህርትና ስብከት መኖሩ መልካም ነው ፥ ይዘቱ ገበያ መር እና ብሽሽቃዊ እስካልሆነ ድረስ ። ጥሩ ስብከት ይዘቱ ከሥርዓተ አምልኮው ሊርቅ አይችልም ፥ ሰማዕያኑንም ወደ ሥርዓተ አምልኮው ላይመራ አይችልም ። ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ መዝሙርን እና ስብከትን ሳነሣ በዚህ ዓውድ መሆኑን እንድትረዱልኝ አሳስባለሁ ።)

በዘመናችን አብዛኛው ምእመን ቤተ ክርስቲያንን የሚያውቃት በዘመናዊ ዝማሬዎች አማካይነት ነው ። ስለዚህም በመዝሙሮቹ ይዘት ልክ ጥልቀት የሌለው እና በዘመናችን ብሽሽቃዊ ዕቅበተ እምነት የተቃኘ ነገረ ሃይማኖታዊ መረዳት እንዲሰፍን ሆኗል ። ይህ ሒደት ደግሞ በአንድ በኩል ከላይ እንደጠቀስሁት በዘመናችን ከሥርዓተ አምልኮው የላቀ ሱታፌ በሚታይባቸው እና በዘመናውያኑ ዝማሬዎችና ስብከቶች በተሞሉት የሠርከ ፣ የእሑድ እና ልዩ ልዩ ጉባኤያት እና ጉዞዎች አማካይነት እየዳበረ ይገኛል ። በሌላ በኩል ደግሞ በዘመናዊው ማኅበራዊ እና ኤሌክትሮኒክ ሚዲያ አማካይነት በየቤታችን የሚገኝ ሆኗል ። ሥርዓተ አምልኮውም ለምእመኑ ነገረ ሃይማኖታዊ መረዳት ያለው አበርክቶ በዚያው መጠን እንዲመነምን ሆኗል ። ኢጃትም ሥርዓተ አምልኮውን በሚገዳደር መልኩ ዘመናዊውን መዝሙር ማዕከል ያደረገን ሁነት በማስተዋወቁ ይህን ሒደት ነው ብዙ እርምጃ ወደፊት እያራመደ ያለው ።

ይህ ጽሑፍም የአእላፋት ዝማሬን ጉዳይ ያደረገው የዚህ ባሕል ተወካይ በመሆኑ እንጂ የአእላፋት ዝማሬን የተነጠለ እንድ ዐዲስ ነገርን ያስተዋወቀ ሁነት አድርጎ በመቁጠር አይደለም ። ይልቁንም ለረዥም ዘመን ሲያድግ የቆየው የዚህ ባሕል ፍሬ ነው ። ነገር ግን ያገኘው ተቀባይነት እና ስኬት ተደርጎ መቆጠሩ ችግሩ ምን ያህል ሥር መስደዱን ስለሚያሳይ ነው ለዚህ ነገር ቀዳሚ ማሳያ አድርገን የወሰድነው ።

※ ※ ※

የአእላፋት ዝማሬ በሥርዓተ አምልኮው ከምናውቀው የበዓል አከባበር የሚለይበት ሌላው ገጹ ፥ በየደብሩ ሳይሆን በየከተማው በአንድ ቦታ ብቻ የሚከናወን መሆኑ ነው ። በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ፥ ዐበይት የሚባሉ በዓላት በሁሉም ደብሮች ይከበራሉ እንጂ ፥ አንድ ቦታ በተለየ መልኩ አይከበሩም ። በየቦታው ልዩ ልዩ ይትበሃል ይኖር ይሆናል ። በመሠረቱ ግን ቅርጹም ሆነ ይዘቱ ተመሳሳይ ነው የሚሆነው ። ይህ የአእላፋት ዝማሬ አካሔድ ከየት የተገኘ ነው ?

ከላይ እንዳልሁት እኔ የአእላፋት ዝማሬ በየደብሩም ሆነ በአንድ ቦታ መደረግ የለበትም ባይ ነኝ ። ነገር ግን ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጥራት ዓላማ ያለው ሁነት ማዘጋጀት ከተፈለገ ቢያንስ ነገሩን በየደብሩ ማካሔድ ይቻል ነበር ። ይህ ቢያንስ ለቤተ ክርስቲያን ትውፊት የተሻለ ይቀርብ ነበር ።

ነገር ግን የአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆች ሁነቱ ከተማ አቀፍ መሆን አለበት ባዮች ናቸው ። ይህም ብቻ አይደለም ፥ ሁነቱ በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ኢጃት ወይም ከኢጃት ፈቃድ ያገኘ አካል ብቻ ሊያዘጋጀው የሚችለው አድርገውታል ። በመጀመሪያው ዙር የአእላፋት ዝማሬ ተደስተውና በቀጣዩ ለመካፈል ሽተው ነገር ግን ከአዲስ አበባና ከድሬዳዋ ርቀው ስለሚኖሩ ያልቻሉ ወጣቶች በሁለተኛው ዙር በያሉበት ከተማ ተመሳሳይ ሁነቶችን ለማዘጋጀት ማሰባቸው ሲሰማ ፥ ኢጃት ይህን ከማድረግ እንዲቆጠቡ ነበር ያሳሰባቸው ።

ኢጃት በመግለጫው ለዚህ እገዳ የሰጠው ምክንያት “የአእላፋት ዝማሬ ስሙ እንደሚያሳየው አእላፋትን የሚያሳትፍ ዝግጅት በመሆኑ በከተማ ደረጃ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ተባርኮ እንዲደረግና የአንድን ከተማ ሕዝብ በነቂስ ማሳተፍ በሚችል ደረጃ እንዲከናወን የታሰበ ዝግጅት ነው ። የአእላፋት ዝማሬን ደረጃ ባልጠበቀ ዝግጅትና በተከፋፈለ አጥቢያ የሚጀመር ከሆነ

ግን ለወደፊቱም በዚያ ከተማ ‘የአእላፋት ዝማሬ’ እንዳይደረግ እንቅፋት ይሆናል ።” የሚል ነው ።

ስለዚህ እንደ አዘጋጆቹ ከሆነ የሁነቱ ዋነኛ መገለጫ ይዘቱ ሳይሆን (በዚሁ መግለጫቸው ዝቅ ብለው “ተመሳሳይ የዝማሬ ዝግጅት የሚያደርጉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የጉባኤውን ርእስ ከልደት ጋር በተያያዙ ሌሎች ስያሜዎች ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል ።” ይላሉና) የሚሳተፈው ሰው ብዛት (ድምቀቱ) እና “ደረጃውን መጠበቁ” ናቸው ።

ማኅሌትም ሆነ ቅዳሴ ፥ ጥምቀትም ሆነ ደመራ ሲደምቁ ደስ ሊለን ይችላል ። ነገር ግን ካልደመቀ አይሆንም የሚባሉ አይደሉም ። የአደባባይ በዓላት የምንላቸው እና በድምቀታቸው የሚታወቁት ደመራ እና ጥምቀት ሳይቀሩ እንዲህ አይነት መሥፈርት የለባቸውም ። እንዲያውም አሁን አሁን እውነተኛ ጣዕማቸውና ለዛቸውን ማጣት የጀመሩት እንዲያ ያለ ድምቀታቸው ላይ ያተኮረ አመለካከት እና አከባበር ከዳበረ ወዲህ ነው ።

በመሠረቱ አንድ በዓል ደመቀ ማለት ክርስቲያኖች በብዛት ወጥተው አከበሩት ማለት ስለሆነ የሚያስደስት ነው ። ነገር ግን እንዲደምቁ ሲባል የሚደረግ የተለየ ጥረት የለም ፤ መኖርም የለበትም ። ለምሳሌ ጥምቀት የበለጠ እንዲደምቅና መከፋፈል እንዳይፈጠር ሲባል በአዲስ አበባ ጃን ሜዳ ብቻ ይከበር አይባልም ። ይልቁንም ለሰዉ ሱታፌ ሲባል በየአካባቢው ይከበራል እንጂ ። የአእላፋት ዝማሬም ፥ ለምሳሌ ፥ በተመሳሳይ ይዘት በየደብሩ ቢደረግ (በየደብሩም ቢሆን መደረግ የለበትም እንጂ) ለየሰዉ ከመቅረቡ የተነሣ የበለጠ ቁጥር ያለውን ሰው የማሳተፍ ዕድል ሊኖረው ይችል ነበር ። ነገር ግን በተቃራኒው ወደየሰዉ ደጅ በቀረበ ቁጥር ድምቀቱ ይቀንሳል የሚል ሐሳብ ነው በአዘጋጆቹ ዘንድ ያለው ። ምክንያቱም የዝማሬው መስሕብ ዝማሬነቱ ሳይሆን “የአእላፋት” መሆኑ ፥ የደመቀ ሁነት መሆኑ ነውና ።

እንዲሁም ፥ የትኛውም በዓል ወይም አገልግሎት በሥርዓት መከናወኑ እንጂ “ደረጃውን የጠበቀ” መሆኑ ጉዳይ ሆኖ አያውቅም ፤ ሊሆንም አይገባም ። “ደረጃ መጠበቅ” እና ሥርዓት መጠበቅ ፍጹም የተለያዩ ነገሮች ናቸው ። ለምሳሌ ቅዳሴን የሚያህል ክቡር ነገር እንኳን ምእመናን ባሉበት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በሌለበት ቦታ ቢደረግ እንኳን ደረጃውን ስለማይጠብቅ ይቅር አይባልም ። ሌላው ቀርቶ አምስት ልዑካን እንኳን መገኘት ባይችሉ በአንድ ቄስና በአንድ ዲያቆን ይቀደሳል ። ግን ምንም ያህል በተጎሳቆለ ሁኔታ ቢቀደስ ፥ ቅዳሴው ከቅዳሴነቱ አይጎድልም ። ስጦታውም በሌላ ቦታ ከሚሰጠው አያንስም ።

የአእላፋት ዝማሬ ግን ከመድመቅ በተጨማሪ ፥ “ደረጃውን መጠበቅም” አለበት ። በየደብሩ ዝማሬውን ማካሔድ ደግሞ ይህን ለማድረግ አይመችም ። እነዚህ ደረጃዎች ምን እንደሆኑ አዘጋጆቹ በግልጽ አልነገሩንም ። ነገር ግን በመግለጫቸውና በሌሎችም ንግግሮቻቸው ሲገልጡ እንደሰማነው ፥ በስፒከርና በስክሪኖች የታጀበ መሆኑ ፣ በእነዚህ ስፒከሮችና ስክሪኖች አማካይነት የተላለፈው ድምፅና ምስል ጥራት ፣ ከጳጳሳት ጀምሮ ብዙ ዘማርያን ፣ አርቲስቶች እና ሌሎችም ታዋቂ ሰዎች መታደማቸው እና የመሳሰሉት ነገሮች ነበሩ ሁነቱ “የተሳካ” እንደነበረ ምስክር ተደርገው የተጠሩት ፥ እነዚህ ሳይሆኑ አይቀሩም ።

ኢጃት የአእላፋት ዝማሬን በራሱ ስም ማስመዝገቡም ሌላው አስገራሚ ነገር ነው ። ሥርዓታዊ በሆነው አምልኮ ውስጥ እንዲህ ያለ አሠራር ፈጽሞ የለም ። ለምሳሌ አባ ጽጌ ድንግል ማኅሌተ ጽጌን ሲደርስ ሐሳቡ በተቻለ መጠን በሁሉም ደብሮች ይቆም ዘንድ ነው እንጂ እርሱ ባለበት አጥቢያ ብቻ ፣ ወይም እርሱ ፈቃድ በሰጣቸው አጥቢያዎች እና ግለሰቦች ፣ እሱ በመሠረተው ማኅበር አስተባባሪነት ብቻ እንዲቆም አይደለም ። አንዴ ከደረሰው በኋላ ባለቤትነቱን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል ። ኢጃት ግን በተቃራኒው ሌሎች ይህን ዐዲስ የበዓል አከባበር በያሉበት እንዲያከናውኑ አይፈልግም ። ይልቁንም ባለቤትነቱን በሕግ አረጋግጦ ይህን ሊያደርጉ የሚሞክሩትን ‘በሕግ አምላክ’ አላቸው እንጂ ።

እነዚህ ኢጃት ያስተዋወቃቸው መስፈርቶች እና አሠራሮች የአእላፋት ዝማሬ ትውፊታዊ እና ሥርዓታዊ ከሆነው የአገልግሎት መንፈስ በእጅጉ የራቁ ለመሆናቸው ምስክሮች ናቸው ። እነዚህ መስፈርቶች እና አሠራሮች ከወዴት የተገኙ ናቸው ? ብለን መጠየቅ ይገባናል ።

ጥሪው በዋናነት ለኮንሰርት ሒያጆች መደረጉ የእነዚህን መስፈርቶች ምንጭ ለማወቅ ጥሩ ፍንጭ ነው ። ምክንያቱም በተለያየ ምክንያት በልደት ዋዜማ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከማይመጣው ሰው ሁሉ ኮንሰርት ሒያጆችን የሚለያቸው እነዚህን ሁለት ነገሮች ፈልገው ወደ ኮንሰርት መሔዳቸው ነው ። ኮንሰርትም ፣ የአእላፋት ዝማሬም እንዲህ ሊገለጹ ይችላሉ ፥ ‘የደመቀ እና ደረጃውን የጠበቀ’ ሁነት ።

እስቲ ነገሩን አንድ በየዓመቱ በልደት ዋዜማ ወደ ኮንሰርት በሚሔድ ሰው ቦታ ሆነን እናስበው ። በልደት ‘ወደ ደብርህ ሔደህ ማኅሌት ቁም ወይም አስቀድስ’ ብትሉኝ ፥ አልሔድም ። እሺ እዚያ ‘በደብርህ ካሉ ሰዎች ጋር በኅብረት ሆነህ በዝማሬ አክብረው’ ብትሉኝም አልሔድም ። ታዲያ ለምን ወደ አእላፋት ዝማሬ እሔዳለሁ ? እዚያ የማላገኘው ፥ እዚህ ግን የማገኘው ምን ስላለ ይሆን ?

ከጥሪው ጀርባ ያለው ሐሳብ ፥ ‘ኮንሰርት የሚሔዱ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ ከኮንሰርት የሚፈልጓቸውን ነገሮች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እናሰናዳላቸው’ የሚል ነው ። ዝማሬው የግድ “የአእላፋት” መሆን ያለበትም ለዚህ ነው ። ድምቀቱን እና “ደረጃውን መጠበቁን” በተመለከተ ያለው ጭንቀት ፣ ጥንቃቄ እና ኩራት ከዚህ ውጭ በሌላ በምንም ሊብራራ አይችልም ። ነገር ግን ድምቀቱ እና “ደረጃው” ሁነቱን ያነሰ እንጂ የበለጠ ክርስቲያናዊ አያደርጉትም ።

የአእላፋት ዝማሬ የቤተ ክርስቲያንን የበዓል አከባበር ታላቁ ሩጫ እና የዘፈን ኮንሰርቶች በሚመዘኑባቸው መስፈርቶች መሠረት የሚለካ ሁነት ነው ። አዘጋጆቹ የአእላፋት ዝማሬን የኢጃት ሕጋዊ ንብረት አድርገው ማስመዝገባቸውም ይህን ነው የሚመሰክረው ። እንዲህ ያለው ሕጋዊ ባለቤትነት እና ልዩ መብት በኮንሰርቶች እና ታላቁ ሩጫን በመሳሰሉ ሁነቶች እንጂ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ዘንድ ጨርሶ የማይታወቅ ነውና ።

ይህ አካሔድ በአእላፋት ዝማሬ የተጀመረ አለመሆኑን መናገር ይገባኛል ። በዚህ መንገድ መጓዝ ከጀመርን ቆይተናል ። ለዚያም ነው አሁን በአእላፋት ዝማሬ ሲደረግ እንግዳ ያልሆነብን ። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጣዖታዊ የሆነውን አምልኮ ድል ለማድረግ በስብከቷ እና በሰማዕት ደም ከመጋደል በተጨማሪ ከውስጧ እየተገነጠሉ ከሚወጡ እና መንጎቿን ለመንጠቅ ከሚጥሩ መናፍቃን ጋርም መታገል እንደነበረባት ሁሉ ዛሬም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ይህኑ ጣምራ ትግል ስታደርግ ትገኛለች ። በዚህ ጣምራ ትግል ውስጥ አረማዊ በሆነው (ዛሬ secular ብለን የምንጠራው) ዓለምም ሆነ በፕሮቴስታንቶች ፣ በካቶሊኮች እና በሙስሊሞችም በሁለት ዋና ዋና መንገዶች እንፈተናለን ። የመጀመሪያው እና ጎልቶ የሚታየው በቀጥታ አስተምህሮን በተመለከተ በሚደረጉ ክርክሮች በኩል የሚመጣው ነው ። ይህ አባቶች እንዳደረጉት ከሐዋርያት የተገኘውን እውነትና ምስክርነት አስፋፍቶ እና ለሁኔታው እንደሚገባ አበጅቶ በማዘጋጀት የምንወጣው ፈተና ነው ።

ሁለተኛው እና ልብ ሳንለው የምንፈተንበት የሚመስለኝ ደግሞ እነሱ ተጠቅመውበት ስኬታማ ሆነውባቸዋል ብለን የምናስባቸውን መንገዶች በመከተል እንድንመስላቸው የሚቀርብልን ሥውር ፈተና ነው ። ለምሳሌ ያህል አሁን አሁን ፕሮቴስታንቶች ገንዘብን ተገን በማድረግ ብዙዎችን ወደራሳቸው ወገን እየሳቡ እንደሆነ እና እኛ ግን በተቃራኒው ከገንዘብ እና ከሥልጣን በመራቃችን እየተጠቃን እና ሰው እየፈለሰብን መሆኑን ጠቅሶ እኛም ባለ ሀብቶችን ማፍራት እና በኢኮኖሚ መሳሳብ እና መጠቃቀም እንደሚገባን ሲነገር መስማት የተለመደ ሆኗል ። ሙስሊሞችም ከሙስሊሞች ብቻ ገዝተው ግን ለሁሉም በመሸጥ ንግድ ላይ የሚያደርጉትን መጠቃቀም እኛም መተግበር እንደሚገባን በተደጋጋሚ ሰምቻለሁ ። ሃይማኖታዊ ክርክሮችንም በተመለከተ እስልምና ላይ ጥያቄ ሲነሣ እና ክርስቲያኖች ስለ እስልምና የምር የሚያስቡትን ነገር ሲናገሩ በሙስሊሞች ዘንድ የሚሰጠው በቁጣ የተሞላ ምላሽ እስልምና ላይ በነጻነት እንዳይወራ ስላደረገ እኛም ተመሳሳይ አካሔድ በመጠቀም ሃይማኖታችንን “ማስከበር” እንዳለብን የሚያስቡም (እኔ እንዳስተዋልሁት) ጥቂቶች አይደሉም ።

ከዘመናዊ አረማዊ ባሕል (modern secular culture) ጋር በምናደርገው ትግልም በተመሳሳይ ፋክክሮች እንጠመዳለን ። ለምሳሌ ያህል የተለያዩ ድርጅቶች ምርቶቻቸውን እና አገልግሎቶቻቸውን ለማስተዋወቅ ተዋንያንን ፣ ዘፋኞችን ፣ ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የሚታወቁ ሰዎችን ወይም በሌላ ዘርፍ በሕዝብ የታወቁ ሰዎችን እንደሚጠቀሙት ፥ በቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ መንገድ በመጠቀም ሕዝቡን ወደ አንድ ጉባኤ ወይም ሁነት ለመጥራት የሚደረግ ጥረት እናያለን ። ወይም ልክ በኮንሰርቶችና በሌሎች ሁነቶች እንዳለው በቤተ ክርስቲያን ለሚደረጉ ጉባኤዎችም ታዋቂ ዘማሪዎችን እና ሰባኪዎችን በማሰለፍና ጉባኤው ላይ ታላቅ ፣ ልዩ ፣ ወዘተርፈ የሚሉ ቅጽሎችን በመለጠፍ ሰዎችን ለመሳብ ይሞከራል ። እነዚህ ሁሉ ዘመናዊ ከሆነው የንግድ ሥራ ተውሰን ወደ ቤተ ክርስቲያን ያመጣናቸው አሠራሮች ናቸው ። የምንዋስበት ዓላማና የሚያመጡት ውጤትም ከንግድ ጋር የተያያዘ ነው ።

ባለፉት መቶ ዓመታት በሚደረጉ የዕቅበተ ዕምነት እንቅስቃሴዎችም ሆነ በሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ እንዲህ ያለው ፈተና እያየለብን

እንደመጣ እና ከላይ በጠቀስኳቸው እና በሌሎችም መንገዶች እየተሸነፍንበት የመጣን ይመስለኛል ። ለምንናገራቸው እና ለምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ መሠረት ከማድረግ በእጅጉ እያፈነገጥን ነው ። እርግጥ ነው ፥ ይህ ነገር ክርስቲያኖች ሁሌ የምንፈተንበት ነው ። ልዩነቱ አሁን ላይ እንደ ፈተና ሳይሆን እንደ ድል የምናየው ነገር መሆኑ ነው ። ከመስፈርቶቹ እና ከይዘቱ ለመረዳት እንደምንችለው የአእላፋት ዝማሬም ይህኑ አካሔድ ነው ሥራ ላይ እያዋለ ያለው ።

※ ※ ※

ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመጥራት በሚደረገው የተልዕኮ ሥራ ውስጥ አንድ ትልቅ ፈተና አለ ። ይኸውም ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመጥራት ከመክበዱ የተነሣ ፥ ሰዎቹን ጎትቶ ቤተ ክርስቲያን ወዳለችበት ከፍ ከማድረግ ይልቅ ቤተ ክርስቲያንን እነርሱ ወዳሉበት ዝቅ ማድረግ እንደመፍትሔ የመወሰዱ አደጋ ነው ። ይህ አደጋ ደግሞ ሁልጊዜ የነበረ ቢሆንም ፥ በዘመናችን በእጅጉ በርትቷል ። ሕይወታችን ከክርስትና ይልቅ ለቤተ ክርስቲያን ባዕድ በሆኑ ሐሳቦች የተዋቀረ እና ክርስቲያናዊ ባልሆነ አየር ውስጥ መኖር የለመደ ከመሆኑ የተነሣ ከቤተ ክርስቲያን ሰውነት ጋር ራሳችንን አሳክተን መኖር ሥቃይ ይፈጥርብናል ፤ ክርስቲያናዊ ወደ ሆነው ከባቢ ስንገባ መንፈሳችን ከባሕር እንደ ወጣ አሳ ይጨነቃል ፤ ያጣጥራል ። ይህ የትውልዱ መገለጫ ነው ። በተለይ በከተማ ያደገ እና የሚኖር ፥ በዘመናዊው ትምህርት የተቀረጸ እና ለኢንተርኔት እና ለማኅበራዊ ሚዲያ የተጋለጠ ሆኖ ይህን ጠባይዕ ያላዳበረ ሰው መኖሩን እጠራጠራለሁ ።

ስለዚህም ፥ ከቤተ ክርስቲያን ውቅር ጋር ለማስማማት ሲባል የራሳችንን ውቅር መለወጥ ሥቃዩ የበዛ ስለሚሆንብን ፥ ይህን ሥቃይ ለመቀነስ የቤተ ክርስቲያንን ሰውነት በእኛ ውቅር መሠረት የማስተካከል ፈተና ይመጣብናል ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው አየር እንዳያፍነን ፥ በሯን ከፍተን የውጭውን አየር በትንሽ በትንሹም ቢሆን ወደ ውስጧ ለማስገባት እንፈተናለን ። የፈተናው መጨረሻ ቤተ ክርስቲያንን ማንነቷን ማሳጣት ነው ። በጣም አሳዛኙ ነገር ደግሞ ይህን እያደረግን ሳለን አሁንም ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንደሆንን ስለምናምን ጥፋታችንን ፈጽሞ አለማስተዋላችን ነው ።

የአእላፋት አማሬ ኢኦርቶዶክሳዊ የሆነበት ሌላው መንገድም ይህ ነው ። ሰዎች ፥ በተለይም ልደተ ጥምቀትን ያገኙ ሰዎች ፥ ከቤተ ክርስቲያን ርቀው እየኖሩ መሆናቸው በእጅጉ ያስቆጫል ። ስለዚህ ነገር ለቤተ ክርስቲያን መቅናትም ይገባል ። እውነት ነው ፥ ሰዎች የጌታን ልደት ምክንያት አድርገው የጭፈራ እና የዘፈን ድግስ ማዘጋጀታቸው እና ብዙ ክርስቲያኖችም በዚያ መታደማቸው ለደረስንበት የግርምቢጣዊነት ጥግ ፥ ‘ኦርቶዶክሳውያን ነን’ ማለታችንም ጨርሶ የይስሙላ እየሆነ ለመምጣቱ ጥሩ ማሳያ ነው ። ነገር ግን ይህም ቢሆን ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን የተነጠለ ሕይወት የመኖራቸው አንድ መገለጫ ነው እንጂ ይህን ነገር ብቻ ቢተዉ መንገዳቸውን አስተካከሉ ማለት አይደለም ። ስለዚህ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጡ ዘንድ የምናደርገው ጥሪ ጠቅላላ የሕይወት መንገድን የሚመለከት እንጂ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን የመራቃቸውን አንድ መገለጫ መገዳደርን መሠረት ያደረገ መሆን የለበትም ።

ቤተ ክርስቲያን ከጥንትም ጀምሮ በዓልን ስታከብር ክርስቲያኖችን ሁሉ ወደ በዓሉ ትጠራለች እንጂ ለይታ የምትጠራው አካል የለም ። ሕዝባውያንን እንኳን ክርስትናን ተረድተው እና ተጠምቀው ወደ ቅዳሴዋ እንዲገቡ ታደርጋለች እንጂ የተለየ የበዓል አከባበር አትሠራላቸውም ። ከእርሷ የራቁትን ክርስቲያኖችም ቢሆን ወደ ንሥሐ ጠርታ ፥ ከዚያ ወደ ምሥጢሯ ታስገባቸዋለች ። ኮንሰርት እና ጭፈራ መጥፎ ነገር ከሆነ ፥ በልደት ብቻ ሳይሆን ሁሌም መጥፎ ስለሆነ ሰዎችን በጠቅላላው በንስሐ እንዲመለሱ እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ያለ ጥሪ እናደርጋለን እንጂ በአንድ ዕለት ብቻ አንጠራቸውም ። ልደትን አስመልክተው ያልተገባ ሥራ ለሚሠሩ ምእመናን የተለየ ተግሣጽ ይገባል እንጂ እንዴት ‘ከእኔ የራቃችሁት ድምቀት እና ከፍ ያለ ደረጃ ፈልጋችሁ ከሆነ እኔ አዘጋጅላችኋለሁ ኑ’ የሚል ጥሪ ይቀርባል ? ቤተ ክርስቲያን ኃጥአንን ወደ ንሥሐ የመጥራት እንጂ ወደ ኃጢአት የሚመራቸውን ፍላጎት ከእርሷ ሳይርቁ የሚወጡበት ዓውድ የማመቻቸት ተልዕኮ ነው እንዴ ያላት ? ልዩ ልዩ ጾር ያለባቸውን ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመጥራት እነዚህን ጾሮች ማዕከል ያደረጉ ልዩ ልዩ የበዓል አከባበሮችን እንፈጥራለን ?

ሰዎች ወደ ጭፈራ የሚሔዱት ቤተ ክርስቲያንን እና በእርሷ ያለውን ፍጹማዊ ደስታ ስላላወቁ ነው ወይስ በቤተ ክርስቲያን ያለውን ስጦታ ንቀው ጭፈራን ስለመረጡ ነው ? ወደ ጭፈራና ወደ ኮንሰርት የሔዱ ሰዎች ወዲያ የሔዱት የልደትን ትርጉም ስላላወቁት ፥ የበዓልን ትርጉም ስላላወቁት ፥ የክርስትና ምንነት

ስላልገባቸው እና ቤተ ክርስቲያን በስሙ ለሚያምኑ ያዘጋጀችው “ዐይን ያላየው ፣ ጆሮ ያልሰማው ፣ በሰውም ልቡና ያልታሰበ”[3] ስጦታ እንዳለ ስላላወቁ ከሆነ ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጡ ዘንድ ይህን እንዲያውቁ ነው ማድረግ ያለብን ። ይህን የምር ሲረዱ አሁን ባሉበት መንገድ የመቀጠል ዕድላቸው ጠባብ ነው ። በተቃራኒው ይህን ሁሉ ዐውቀውና ንቀው ከሆነ ወደ ሌላ ቦታ የሔዱት ፥ ልቡናቸው እንዲመለስ ከመጸለይ ሌላ ማድረግ የምንችለው ብዙ ነገር አይኖርም ።

እኔ እንደምረዳው ፥ እውነተኛው የክርስትና ምንነት እና የቤተ ክርስቲያን ማንነት ከብዙዎቻችን የተሰወረ ነው ። ለአንዳንዶቻችን ደግሞ ከሌሎቻችን ይልቅ ሩቅ ነው ። ለምሳሌ እኔ ራሴ በዓል ማለት ትንሣኤም ሆነ ልደት ከመብላት እና ከመጠጣት እና ዘመድ ከመጎብኘት ያለፈ ትርጉም የነበረው የማይመስለኝ ጊዜ ነበር ። አሁን ግን ከዚያ የተሻለ አውቃለሁ ። በበዓል ወደ ኮንሰርት ለሚሔዱም ሰዎች መሔዳቸው ፥ በተለይ የጥምቀት ልጅነት ያላቸው ክርስቲያኖች ሲሆኑ ፥ እንዲህ ካለው ርቀትና አለመረዳት የመነጨ ነው ብዬ ነው የማስበው ።

ያ ከሆነ እነዚህን ሰዎች እንዴት ነው መጥራት የሚገባን ፥ የቤተ ክርስቲያንን እውነተኛ ማንነት በመግለጥ ፣ በማስተማር የጌታ በሆነው በዓል ወደ ጌታ ደስታ እንዲገቡ በማድረግ ነው ? ወይስ እውነተኛውን ሐሴት ባለማወቅ የሻቱትን ከንቱ የሆነውን ፥ ሰውነትን የሚያረክሰውን ደስታ የሚተካ ሁነት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማዘጋጀት ነው ? እንግዲያውስ ለምን ሥጋ መብላት ስለሚወዱ የማይጾሙ ሰዎችን ድል ያለ የጾም ቡፌ በማዘጋጀት ወደ ቤተ ክርስቲያን አንጠራቸውም ?

ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም ወደ ራሷ ስትጠራ ከዚያ በኋላ ዘወትር የጌታን ትእዛዛት በመጠበቅ እንዲኖር እና ይህን ለማድረግ በሚደረገውም ጥረት የሚኖረውን መውደቅና ማደፍ ዘወትር በንሥሐ እየታጠበ በምሥጢራት ይጸና ዘንድ ነው ። ጥሪዋ የዘወትር እንጂ ፥ አንድ ያልተገባን ነገር የተመለከተ እና ለአንድ ጊዜ የሚደረግ ፥ ምላሹም አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ አይደለም ።

ይህን በተመለከተ የአእላፋት ዝማሬን የሚከላከሉ ሰዎች የሚያቀርቡት አንዱ መከራከሪያ ‘ሰዎችን በመጀመሪያ የሚፈልጉትን ነገር አሳይቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥራትና ቀስ ብሎ በሒደት ሥርዓታዊ ወደ ሆነው አምልኮ እና ወደ ምሥጢራት ማቅረብ ይቻላል ፥ ይገባልም’ የሚል ነው ። የአእላፋት ዝማሬን እንዲህ ያለ መንገድ አድርገው ነው የሚረዱት ።

ይህ መከራከሪያ እጅግ ስሑት ፥ እጅግም አደገኛ ነው ። በመጀመሪያ እና በመሠረቱ ፥ ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የተቃረነ ነው ። ሰዎችን ክርስቲያን ማድረግን ወገንን ማብዛት እንጂ መስቀልን መሸከም እና ሌሎችንም ወደ መስቀል መጥራት አድርጎ ካለመመልከት የሚመጣ ነው ። ሰዎችን አታልሎ ክርስቲያን የማድረግ መንገድ ነው ። ይህም ጌታችን በወንጌል ካስተማረውና ካደረገው ሁሉ የተቃረነ ነው ። ክርስትና ጠባብ መንገድ ፣ ጠባብ በር ፣ ሁሉን ነገር ትቶ ክርስቶስን መከተል እንጂ ሰዎች በከረሜላ እየተባበሉ የሚቀላቀሉት ኅብረት አይደለም ።

ጌታችን ሁለት አሳ እና አምስት እንጀራ አበርክቶ ያበላቸው ሰዎች በማግስቱ እየፈለጉት ወደ ቅፍርናሆም በመጡ ጊዜ የምር እርሱን ፈልገው ሳይሆን እንጀራውን ፈልገው እንደመጡ ነገራቸው ። ነገር ግን የሚጠፋ ያይደለ እውነተኛ የሕይወት እንጀራ እርሱ እንደሆነ እና የእርሱን ሥጋ እና ደም መብላትና መጠጣት እንዳለባቸው ሲነግራቸው ሁሉም ጥለውት ተበተኑ ። ጌታችን በመጀመሪያም እንጀራውን ያበላቸው እንጀራው ስለሚያስፈልጋቸውና መራባቸውን አይቶ ስላዘነላቸው እንጂ ስለ እንጀራው ብለው እንዲከተሉት አልነበረም ። ለዚህም ነው እንጀራውን ፈልገው የመጡትን ‘እንጀራ አበርክቼ እያበላሁ ተከታዮቼ አደርጋቸዋለሁ’ ብሎ ያልተቀበላቸው ። ይልቁንም ስለ እንጀራው ብለው እንዳይከተሉት አገዳቸው ። የሚከተሉት ከሆነ ፥ ‘ይህን ማን ሊሰማው ይችላል’ ያሉትን እና ጭንቅ የሆነባቸውን እውነት ፈልገው እንዲከተሉት ነገራቸው ። እነርሱም ትተውት ሔዱ ። እኛም በፊታችን ያለው ምርጫ ተመሳሳይ ነው ።

ደግሞም ይህ መርሕ (አልባነት) በሥራ ላይ ሲውል የሚኖረው ውጤት ይኖረዋል ተብሎ ከሚታሰበው ተቃራኒ ነው ። መጀመሪያ የሚያስፈልገውን ነገር ሽቶ ሳይሆን የሚፈልገው ነገር ቀርቦለት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣ ሰው ፥ ያን ፈልጎ የመጣውን ነገር ባጣ ቅጽበት ቤተ ክርስቲያንን ትቶ የመሔዱ ዕድል ሰፊ ነው ። በቤተ ክርስቲያን አለ በሚባልበት ጊዜም እንኳን የምር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የለም ። ምክንያቱም በልቡ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን ያ ፈልጎ የመጣው ነገር ነው ። አንድም ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከታት (የሲ. ኤስ. ሊዊስን አገላለጽ ለመዋስ) የሚያስፈልገውን ነገር

---

[3] ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ ፣ ቁ. 36

ቢጣፍጥም ቢመርም እንደምታቀርብለት እናቱ ሳይሆን የፈለገውን ሁሉ እንደማትከለክለው አያቱ ስለሚሆን በየቀኑ ከእርሷ የሚፈልጋቸውን ነገሮች የሚጠይቅና ፥ በተከለከለ ጊዜ የሚያማርርና ጥሏት ለመሔድ የሚዝት ፥ የሚሔድም ሰው ይሆናል ።

ምን ያህል ኮንሰርት ይሔድ የነበረ ሰው ኮንሰርቱን ትቶ ወደ አእላፋት ዝማሬ እንደመጣ አላውቅም ። ነገር ግን የመጡ ሰዎች እንደሚኖሩ አምናለሁ ። እነዚህ ሰዎች በሚቀጥለው ዓመት የአእላፋት ዝማሬ ድምቀቱ ቢደበዝዝና ደረጃው ቢወርድ ወደ ኮንሰርታቸው ቢመለሱ ይፈረድባቸዋል ? ምክንያቱም መጀመሪያም የተጠሩበት ምክንያት ድምቀቱና ከፍ ያለ "ደረጃው" ነበርና ።

ሌላው ይህን መከራከሪያ የሚያቀርቡ ሰዎች የሚስቱት ነገር ፥ ይህ መንገድ ብዙዎችን ይስባል ብለው የሚያስቡትን ያህል ብዙዎችን ከውስጥ ሊገፋ እንደሚችል እና ከውጪም እንዳይመጡ እንደሚያደርግ ነው ። ከላይ እንዳልሁት ጥሪው ክርስቲያናዊ ካለመሆኑ የተነሣ ይህ ዓይነቱን ጥሪ የሚቃወሙት መምህራን እና ምእመናን ይገፋሉ ። በሌላ በኩል ከውጭ ሆነው ከልባቸው ቤተ ክርስቲያንን የሚፈልጓት ሰዎች በዚህ ዓይነቱ ድምቀት ላይ የተመሠረተ ጥሪ ቤተ ክርስቲያን ከዓይናቸው ትጋረዳለች ። ቢመጡ እንኳን የፈለጉትን ሰላም ፥ ከሥርዓታዊው ሥርዓተ አምልኮና ከምሥጢራት የሚገኘውን ሰላም ፥ ከአእላፋት ዝማሬ ወይም ከሌሎች መሰል ሁነቶች አያገኙትም ። ስለዚህ ከልባቸው ቤተ ክርስቲያንን የሚሿትን እየገፋን ፥ ቤተ ክርስቲያንን የድምቀት ቦታ እና ከሰዎች ጋር መስተጋብር መፍጠሪያ ዓውድ (social circle) አድርገው የሚያዩዋትን እንጠራለን ።

እንዲህ የምለው ቤተ ክርስቲያንን ብዙ ጊዜ እንደ ቦታ ስለምናስባት ነው እንጂ ፥ ፍጹም በሆነው ማንነቷ የክርስቶስ አካል አድርገን ስናያት እና እያንዳንዱ ክርስቲያን አባሏ (አካሏ) መሆኑን ስናስተውል ፥ ይህ መንገድ የተወሰኑ ሰዎችን ከቤተ ክርስቲያን የሚገፋ ሳይሆን ራሷን ቤተ ክርስቲያንን የሚያጎድላት ነው ።

ቅድም እንዳልሁት ለባለጋራዎቻችን "ስኬት" አስገኝቶላቸዋል ብለን የምናስበውን መንገድ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ትውፊት አንጻር ሳንመዝን ሥራ ላይ የማዋል ልማዳችን ይመስለኛል ለዚህ የዳረገን ። ከላይ እንዳልሁት ኮንሰርቶችን እና ሌሎች ብዙ ሰው የማሳተፍ ዓላማ ያላቸው ሁነቶችን የሚያዘጋጁ ሰዎች ስኬታቸውን በዋናነት የሚለኩት በተሰበሰበው ሰው ብዛት እንደመሆኑ ብዙ ሰው ለመሳብ የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ ። በፕሮቴስታንቶች ዘንድም ይኸው አካሔድ የተለመደ ነው ። ብዙ ፕሮቴስታንቶች ስኬታቸውን የሚለኩት እሑድ እሑድ በአዳራሾቻቸው በሚሰበሰበው ሰው ብዛት እና አንዳንዶቹም በሚያገኙት የገንዘብ ብዛት ስለሚለኩ ለሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር ከመስበክ ይልቅ ሰዎች የሚፈልጓቸውን ነገሮች ይሰብካሉ ። ይህ አካሔድ ነው የብልጽግና ወንጌል የሚባል ፈጽሞ ከክርስትና የሚቃረንን "ክርስትና" እስከመውለድ የደረሰው ። የአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆችም ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመጥራት አመቺ መንገድ እንዳገኙ በማመን ከውጭ ሲታይ ከድምቀቱ የተነሣ "ስኬታማ" የተልዕኮ እና "የሕዝብ ግንኙነት" ሥራ ተብሎ ሊገለጥ የሚችልን ፣ በክርስቲያናዊ መነጽር ሲታይ ግን ከባድ ጥፋት የሚያስከትልን ጎዳና እየተከተሉ ነው ።

ሌላው ማንሣት ያለብኝ ነጥብ ፥ ከአእላፋት ዝማሬ ጋር በተያያዘ ይህ መከራከሪያ ሲነሣ የአእላፋት ዝማሬ ምንነትም የሚለወጥ መሆኑን ነው ። እንዲህ ያለው መከራከሪያ የአእላፋት ዝማሬ ከላይ እስከታች ፣ ከውስጥ እስከውጭ ኦርቶዶክሳዊ ሁነት መሆኑ ቀርቶ ፥ ሰዎች የምር ኦርቶዶክሳዊ ወደሆነው ነገር ለመግባት እስኪችሉ ማቆያ ፥ በይዘቱም የሰዎችን ፍላጎት ያማከለ መሆኑን ያሳብቃል ። ምክንያቱም ስለ ማኅሌት ወይም ስለ ቅዳሴ ተመሳሳይ ነጥብ ሊነሣ አይችልምና ። ማኅሌትንም ሆነ ቅዳሴን ሥርዓቱን ጠብቆ ከልቡ የሚሳተፍ ሰው ፈጽሞ የቤተ ክርስቲያን ተካፋይ ሆኗል እንጂ እነሱን ተሻግሮ ሊያየው የሚገባው ፥ ላለማስደንገጥ ወይም ላለማስፈራራት ተብሎ የተሸሸገው ምንም ነገር የለም ።

ስለ 'የአእላፋት ዝማሬ' ግን 'ሰዎችን የሚፈልጉትን አሳይቶ የማቅረብ ዘዴ ነው' የሚል መከራከሪያ የምናነሣ ከሆነ የአእላፋት ዝማሬ ሲብስ የማያስፈልግ ፣ ከቤተ ክርስቲያን በአፍአ ያለ ሁነት ፥ ሲሻል ደግሞ ሁሉም ሰው ወደ ማኅሌትና ወደ ቅዳሴ እስኪገባ ድረስ መተላለፊያ የሚሆን ከንዑሰ ክርስቲያንም ላነሱ ለሕዝባውያን የተዘጋጀ ግብር ነው ማለት ነው ፤ ንዑስ ክርስቲያን እንኳን ቅዳሴውን ወንጌል እስከሚነበብ ድረስ ይሳተፋሉና ። ቅዳሴን በከፊልም ቢሆን መሳተፍ የጀመረ ሰው ደግሞ ቀድሞውኑም ወደ ቤተ ክርስቲያን ማዕከል መጥቷልና ለምን የማቆያነት ሚና ወዳለው ወደ አእላፋት ዝማሬ መሔድ ያስፈልገዋል ?

※ ※ ※

የአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆች ለሁነቱ ካስቀመጡት ግብ አንጻር ግርምቢጣዊ የሆነው አንዱ ሁናቴ ፥ ከአእላፋት ዝማሬ መጀመር በኋላ የገና እና የማኅሌት ሱታፌ በብዙ ደብሮች ቀንሶ መታየቱ ነው ። ብዙዎች ማኅሌት ከመሔድና ከማስቀደስ ይልቅ የአእላፋት ዝማሬ ላይ መታደምን መርጠዋል ። ይህን እንዴት እንረዳው ?

ከላይ የተነሣውን 'የአእላፋት ዝማሬ ሰዎችን ቀስ ብሎ እና የሚፈልጉትን ነገር በመስጠት ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጥራት መንገድ ነው' የሚል መከራከሪያ አንጻር ካየነው እነዚህ ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን መሃል ወደ ዳር እየሔዱ ነው ማለት ሊሆን ነው ። ወይም ደግሞ ወደ አእላፋት ዝማሬ የኮበለሉት ሰዎች በማኅሌቱና በቅዳሴው በአካል እንጂ በኅሊና ቀድሞውኑም አልተገኙምና ፥ ምሥጢሩም በአጠገባቸው ራሱ አላለፈምና የአእላፋት ዝማሬ የተጫወተው ሚና ይህን እውነታ ገሃዳዊ ማድረግ ብቻ ነው ልንልም እንችላለን ።

ነገር ግን ይህን ሁናቴ በተመለከተ ምናልባት ቀድሞውኑም ሰዎችን ወደ ማኅሌት መጥራት ያልተቻለው ወይም ያልተፈለገው ፥ ኋላም ብዙዎች ከማኅሌትና ከቅዳሴ ቀርተው ወደ አእላፋት ዝማሬ የሔዱት ፥ ማኅሌቱን እና ቅዳሴውን ለመረዳት ለብዙዎች አስቸጋሪ ስለሚሆንባቸው ነው የሚል መከራከሪያ እንደሚኖር እገምታለሁ ። ይህ በጣም ጥሩ ነጥብ ነው ። ነገር ግን ከላይ እንዳልሁት ይህን ችግር መፍታት ያለብን ሥርዓተ አምልኮውን ለምእመኑ ቅርብ በማድረግ ነው እንጂ ከሥርዓተ አምልኮው የሚያርቀው አማራጭ በመስጠት አይደለም ።

የአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆች ማኅሌት ይቆሙ የነበሩ ሰዎች ማኅሌት መቆማቸውን ትተው ወደ እነርሱ እንዲመጡ ጥሪ አላቀረቡም ። እንዲያውም ሰዎች የአእላፋት ዝማሬ በመሔዳቸው ከማኅሌቱ እና ከቅዳሴው የመቅረታቸውን ነገር በማንሣት ለቀረበባቸው ትችት ሰዎች ከዝማሬው በኋላ ወደየደብራቸው በመሔድ ወይም እዚያው የአእላፋት ዝማሬ በተዘጋጀበት ደብር በመቆየት ማኅሌቱን እና ቅዳሴውን እንዲሳተፉ አደራ ብለዋል ።

ይህ አደራ የአእላፋት ዝማሬ ሰዎችን ከኮንሰርት ለመጥራት የተዘጋጀ ነው ከሚለው ማብራሪያ ጋር የሚጣረስ ነው ። ከላይ ከተነሣው ፥ 'ሰዎችን የሚፈልጉትን ነገር አሳይቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ማምጣት' ከሚለው መከራከሪያ ጋርም የሚጋጭ ነው ። ማለትም የሚመጡት ሰዎች ለወትሮው በቅዳሴና ማኅሌት የማይሳተፉ ኮንሰርት ሒያጆች ብቻ ሳይሆኑ እንዲያ ያለ ሱታፌ ያላቸው ሰዎችም ወደ አእላፋት ዝማሬ መጠራታቸውን የሚያሳይ ነው ። ስለዚህ አደራውን የምር ከወሰድነው አዘጋጆቹ የአእላፋት ዝማሬን ያዩት በቤተ ክርስቲያን ባለው አከባበር ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎች እንደተጨማሪ አከባበር አድርገው እንዲታደሙትም እንጂ ከቤተ ክርስቲያን የራቁ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀርቡበት ብቻ አይደለም ማለት ነው ። ያ ከሆነ ግን ቀድሞውኑንም የአእላፋት ዝማሬን የመፈጠር ምክንያት ሰዎችን ከጭፈራ እና ከዘፈን ቦታዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመጥራት ነው ብለው መግለጣቸው ወይ ስህተት ነው ፥ አሊያም ሐሰት ነው ።

መቼም በዓልን በኮንሰርትና በጭፈራ ቦታዎች ያሳልፉ የነበሩት ሰዎች ሊሆኑ አይችሉም ወደ ማኅሌትና ወደ ቅዳሴ እንዲሔዱ ማሳሰቢያ የሚሰጣቸው ። ምክንያቱም ቀድሞውኑም ኢጃት እነዚህን ሰዎች እንዲያ ካሉት ቦታዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመጥራት ልዩ እና የደመቀ ሁነት ያስፈልጋል ብሎ ያመነው ቅዳሴውና ማኅሌቱ ይህን ለማድረግ በቂ ስላልነበሩ ነው ። ስለዚህ ቀድሞ ያልነበረው ድምቀት አሁን ከየት መጥቶ ነው የአእላፋት ዝማሬ ሲያልቅ ድምቀትን ፍለጋ ኮንሰርት መሳተፋቸውን ትተው የመጡት ሰዎች ወደ ማኅሌትና ወደ ቅዳሴ የሚሔዱት ? በተቃራኒው ወደ ማኅሌቱና ወደ ቅዳሴው እንዲሔዱ ጥሪ ከተደረገላቸው ይመጡ ነበር ተብሎ ከታሰበ ደግሞ የአእላፋት ዝማሬ መዘጋጀት አልነበረበትም ። የአእላፋት ዝማሬን ለማዘጋጀት ወራት አስቀድሞ የተደረገው ጥናትም ለቅዳሴውና ለማኅሌቱ መደረግ ይችል ነበር ። ሁነቱን ለማዘጋጀት የፈጀው ጉልበትና ገንዘብም ለዚህ መዋል ይችል ነበር ።

ይህ ሁሉ ተቃርኖ አዘጋጆቹ የሚጠሯቸውን ሰዎች ፣ ምናልባትም ደግሞ ራሳቸውንም ጭምር እያታለሉ እንደሆነ ነው ለእኔ የሚያሳየኝ ። በእውነት ዝማሬውን ያዘጋጁት በጭፈራና በዘፈን ቦታዎች ለነበሩ ሰዎች ከነበረ በየደብሩ ማኅሌት ይቆም እና ያስቀድስ የነበረውን ሰው በግልጽ ወደ አእላፋት ዝማሬ እንዳይመጣ ነው መንገር የነበረባቸው ፥ ዳዊት የደገመውን ሰው መልሰው ፊደል እንደማያስቆጥሩት ሁሉ ። ዝማሬው እንዲህ ላሉት ሰዎችም የተዘጋጀ ከሆነ ደግሞ ለምን ኮንሰርት ሒያጆችን ለዝግጅታቸው ሰበብ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል ?

ሌላው የአደራው ሐሳዊነት ደግሞ የአእላፋት ዝማሬ ራሱ በብዙ ደብራት ከሚካሔደው ማኅሌት እና ቅዳሴ ላይ ሰዎችን ጠርቶ ካመጣ እና በተዘጋጀበት ደብር ያለውንም ማኅሌት በለሆሳስ እንዲደረግ ካደረገ በኋላ መልሶ ሰዎችን

ወደ ማኅሌት መጋበዙ ነው ። ከቀኑ አሥር ሰዓት ጀምሮ እስከ ማታ ሦስት ሰዓት ፥ ማለትም ቢያንስ ማኅሌቱ እስኪጋመስ ድረስ የሚቆይን ሁነት እንዲታደሙ ሰዎችን ከጠሩ በኋላ መልሶ ማኅሌቱን እንዲሳተፉ መጋበዝ ከልቡ የሆነ ሰው የሚያደርገው አይደለም ።

ብርታት ያላቸው ሰዎች ምናልባት ሊያደርጉት የሚችሉ ቢሆንም ፥ የአእላፋት ዝማሬን የተሳተፉ ሰዎች ቅዳሴውንም የመካፈል ዕድላቸውም አነስተኛ እንደሆነ ግልጽ ነው ። አብዛኛው ሰው ብርታቱ አይኖረውም ። ቢኖረው እና ለማስቀደስ ቢፈልግ ራሱ ግን በእጅጉ የማይመች ሁኔታ ውስጥ ነው ራሱን የሚያገኘው ። እዚያው ልቆይም ቢል በኋላ በሌሊት ወደ ቤቱ ለመመለስ ወይ የራሱ መጓጓዣ ሊኖረው ይገባል ፥ አሊያም ብዙ ወጪ ለማውጣት ይገደዳል ። የአእላፋት ዝማሬ እንዳለቀ ወደ ደብሩ ለመመለስም ቢሞክር ቢል ብዙ እንግልት ይገጥመዋል ። ይህን ሁሉ ልቦናቸው አጥቶት አይመስለኝም አዘጋጆቹ ፤ አደራው ለማለት ያህል ብቻ የተባለ ስለሆነ ነው እንጂ ።

የአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆች በመጀመሪያ ነገሩን ሲወጥኑ በዋናነት የታሰባቸው ኮንሰርቶችን የመገዳደር እንጂ የማኅሌትና የቅዳሴው ነገር እንዳልሆነ ግልጽ ነው ። ለዚህም ምስክር የሚሆነው በቅድሚያ ሁነቱን ለማድረግ የታሰበው በመስቀል አደባባይ የነበረ መሆኑ ነው ። መስቀል አደባባይ በመንግሥት በመከልከሉ ነው ሁነቱ ወደ ቦሌ መድኃኔ ዓለም የተዛወረው ። በድሬዳዋም በአደባባይ ነው የተካሔደው ።

ከዚያም በኋላ ደግሞ ሁነቱን የሚታደመው ሰው ከኮንሰርትም ወይም ከማኅሌት መምጣቱ አላሳሰባቸውም ። ያሳሰባቸው ሰዉ ከየትም ይምጣ የሁነቱ መድመቅና ከኮንሰርቶች ወይም ከሌሎች የአደባባይ ሁነቶች በላይ የደመቀ ሆኖ መታየቱ ነው ። ይህ ደግሞ ቀደም ብዬ እንዳልሁት ኦርቶዶክሳዊ ለሆነው ሥርዓተ አምልኮ መለኪያ ተደርጎ ሊቀርብ የሚገባው ነገር አይደለም ።

ያም ሆኖ ግን ብዙ ሰው ማኅሌቱን እና ቅዳሴውን እየተወ ወደ አእላፋት ዝማሬ የፈለሰው በአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆች ግልጽ ጥሪ እንዳልሆነ ልብ ማለት ይገባኛል ። ይህም ምን ያህል አደጋ ላይ እንዳለን ያሳያል ። ኢጃት ኮንሰርት ሒያጆችን ለማማለል ያቀረበው ጥሪ ያማለለው ሰንበት ተማሪዎችን እና ማኅሌት ላይ ይታደሙ የነበሩ ሰዎችን ነው ። ድምቀቱና ደረጃው የታሰበው ኮንሰርቶችን እና ጭፈራ ቤቶችን እንዲያስንቅ ሆኖ ሳለ ግን ማኅሌቱን እና ቅዳሴውን ነው ያስናቀው ። ይህ የሚያሳየው በቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ መደበኛ ሱታፌ በሚያደርጉ እና በተለያዩ አገልግሎቶች ላይ በተሰማሩ ክርስቲያኖች ዘንድ ሳይቀር ኢክርስቲያናዊ የአእምሮ ሥሪት (ድምቀትንና “ከፍ ያለን ደረጃን” መውደድ) ሰፍኖ እንዳለ ነው ።

ምንም እንኳን የአእላፋት ዝማሬ ቅዳሴንና ማኅሌትን ለመተካት ፥ ወይም በእነርሱ ዘንድ የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት ሲባል የተዘጋጀ አይደለም ቢባልም ነገር ግን በግብር እየሆነ ያለው ያ ነው ። ማለትም በሰዉ ልብ ውስጥ የማኅሌትን እና የቅዳሴን ቦታ ነው የሚጋፋውና የሚነጥቀው ። እንዳየነው በማኅሌቱና በቅዳሴው ይሳተፉ የነበሩ ሰዎችም ድምቀቱን ስለሻቱ ወደ አእላፋት ዝማሬ ይመጣሉ ። ከኮንሰርቶችና ከጭፈራ ቦታዎች ገናን ለማክበር ወደዚህ የመጡት ሰዎችም ይህን አልፈው ወደ ማኅሌት የሚሔዱበት ምክንያት አይታየኝም ። የተጠሩት ለድምቀት ነውና ።

ቀደም ብዬ እንዳነሣሁት ፥ በአእላፋት ዝማሬ የሚቀርቡትም ሆነ በጠቅላላው በአሁኑ ወቅት በብዛት የሚሰሙት መዝሙሮችም ሆኑ ስብከቶች በቅዳሴ ፣ በማኅሌትና በሰዓታት ከሚገኘው ይዘት ጋር ለመነጻጸር የሚበቁ አይደሉም ። ነገር ግን ብዙ ሰው በጣም ከፍ ካለው የእምነት መግለጫ እና የአምልኮ ሥርዓት በእጅጉ ወዳነሰው ሔዶ መታደምን ይመርጣል ። ይህ በአንድ በኩል በምእመናን እና በሥርዓተ አምልኮው መካከል ያለውን ርቀት ያሳያል ። በዚህ ረገድ የደረሰብንን ድቀት ያሳያል ። በሌላ በኩል ግን ከእውነተኛ መረዳት ፥ ተመስጦ እና ጥልቅ ነገረ ሃይማኖት ይልቅ ልክ በጭፈራ መድረኮችና በፕሮቴስታንታውያን ዘንድ እንደሚታየው ዓይነት ድምቀትን እና ብልጭልጭታን መውደድ ቤታችንን እንደወረሳትም ያሳያል ። የአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆች ደግሞ ይህን ዝንባሌ ይበልጥ መመገብና ማሳደግ ቀጥለዋል ።

※ ※ ※

የአእላፋት ዝማሬ በቅርጽ ፣ በግብ እና በይዘት ከኖረው የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ጋር ያለው ልዩነት ፥ እንዲሁም ለሥርዓተ አምልኮው ተገዳዳሪ መሆኑ በአጋጣሚ የሆኑ አይደሉም ። ይልቁንም ስሑት ከሆነ ነገረ ሃይማኖታዊ መረዳት የመነጩ ናቸው ። ይህ ስሑት መረዳት ነው ወደ ተግባር ሲቀየር እነዚህን ፍሬዎች ያፈራው ።

ተልዕኮን በተመለከተ የሚታየውን ግልጽ ልዩነት ከላይ አንሥቻለሁ ። ነገር ግን ከዚህም ባሻገር ሁነቱ

በተዘጋጀበት እና በተካሔደበት ሒደት ውስጥ የተገለጡ ነገረ ሃይማኖታዊ ሕጸጾች ነበሩ ። እነዚህ ሕጸጾች የአእላፋት ዝማሬ ከሥርዓተ አምልኮውና ከኖረው ትውፊት በእጅጉ የራቀ መንፈስ እንዳለው ፈጽመው የሚያስረግጡ ሆነው አገኛቸዋለሁ ። ስለዚህም የመጨረሻ ምስክሮቼ አድርጌ አቀርባቸዋለሁ ።

የአእላፋት ዝማሬ ከኮንሰርቶችና ከሌሎች መሰል ሁነቶች የቀዳው አንዱ ነገር ለዝማሬ ከጠራቸው ሰዎች መካከል ለተወሰኑት VIP (ክቡራን) ብሎ ልዩ ቦታ መስጠቱ ነው ። እነዚህ ሰዎች የተሰጣቸው ልዩ ቦታ በሁነቱ ውስጥ ካላቸው የመሪነት ወይም ሌላ ሚና የተነሣ ሳይሆን በማኅበራዊ ሚዲያ ወይም በሌሎች መንገዶች የሚታወቁ ከመሆናቸው የተነሣ ነው ። ልክ እንደሌሎቹ የአእላፋት ዝማሬ ገጾች ሁሉ ይህም በቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ የሌለ ብቻ ሳይሆን የተጠላ ነገር ነው ።

በሥርዓተ አምልኮ ውስጥ ካህናትና ሊቃውንት ለአገልግሎት የሚገባቸውን ቦታ ከመያዛቸው በዘለለ በምእመናን መካከል በዕውቅናም ሆነ በሌላ መሥፈርት መሠረት ልዩነት አይደረግም ። እንዲያውም በተቃራኒው ሀብታም ሰው በሀብቱ ፣ ዝነኛ ሰው በዝናው እንዳይከበር ፣ ድሃም በድህነቱ እንዳይገፋ የተለየ ጥንቃቄ ይደረጋል ። ለምሳሌ ያህል በዲድስቅልያ ከሚገኙት ትእዛዛት አንዱ አንድ ጳጳስ በአገልግሎት ላይ ሳለ በውጭው ዓለም የታወቀ እና የተከበረ ሰው ቢመጣ እሱን ለመቀበል ሲል አገልግሎቱን እንዳያቋርጥ ፣ ይልቁንም ሰውን የሚያከብር መስሎ እንዳይታይ ምንም እንዳልተፈጠረ ሆኖ ተግባሩን እንዲያከናውን ያዘዋል ። በተቃራኒው አንድ ድሃ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ቢገባ ግን በተቃራኒው ያ ሰው የሚገባውን ቦታ ማግኘቱን ሳያረጋግጥ አገልግሎቱን እንዳይቀጥል ፥ የራሱን ቦታ ለዚያ ሰው ለቆ መሬት መቀመጥ ቢኖርበት እንኳን እንዲያደርገው ያዛል ።[4] በዚህ አመክንዮ መሠረት እንዲህ ባሉ አገልግሎቶችና በዓላት ወቅት የተለየ ትኩረት ልናደርግ የሚገባን በሰው ዘንድ ለሚታወቁ እና ለተከበሩ ሰዎች ሳይሆን ሰዎች ላይጠነቀቁላቸው ፣ ሊንቋቸውና ሊገፏቸው የሚችሏቸውን ሰዎች ነው ።

ይህ ትእዛዝ የተሰጠው አንድ ሰው የሚቀመጥበት ቦታ ክብሩን ይገልጥ በነበረበት በሮም መንግሥት ውስጥ ነው ። በሮም መንግሥት ውስጥ ሰው በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ሁሉ የአንድ ሰው ክብር በሚቀመጥበት ቦታ ይገለጣል ። ለአንድ ባለሥልጣን ከዝቅተኞቹ ሹሞች ጋር መቀመጥ ውርደት ነው ። ይህ በእኛም ሀገር የግብር ሥርዓት የሚታይ እንደነበረ ፍቅር እስከ መቃብርን ያነበበ ሊያስታውስ ይችላል ። ክርስቲያን አባቶች ግን ይህን አካሔድ በመገልበጥ ለሚናቁትና ለሚገፉት የበለጠ ክብርን የሚሰጥ ሥርዓት ነበር የሠሩልን ።

የአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆች በቤተ ክርስቲያን ያለውን ሥርዓት ለመከተል ፥ ወይም ከሥርዓቱ የተቃረነ ነገር ላለማድረግ ትንሽ እንኳን ተጠንቅቀው ቢሆን ይህን ለማድረግ ባልደፈሩ ነበር ። ነገር ግን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲያስቡ ውስጣዊ የሆነው አመክንዮ እና መንፈስ ሳይሆን የሚታያቸው ከላይ ከላይ ያለው መገለጫ ብቻ ነው ። ነጭ መልበሱ ፣ ጧፍ ማንደዱ ፣ ቀስ ብሎ ማዜሙ ወዘተርፈ እንጂ እንዲህ ያሉት አስተምህሮው የሚገለጥባቸው ዐበይት ጉዳዮች እምብዛም አያሳስቧቸውም ። ይህ መረዳታቸው መንግሥቱ ለማ በልጅነታቸው ከጓደኞቻቸው ጋር አደረግነው ያሉትን አንድ ሥራ ያስታውሰኛል ። እሳቸውና ጓደኞቻቸው ተሰብስበው በዋናነት በጭቃ ፣ ሌሎች ዕቃዎችንም ጨማምረው አንዲት መኪና ይሠራሉ ። ሐሳባቸው የምር የሚሔድ መኪና ለመሥራት ነው ። የሠሯት መኪና ከውጪ ስትታይ (ከጭቃ ከመሠራቷ በቀር) የሚያውቋቸውን መኪኖች እስክትመስል ለፍተው ሠሯት ። እውነተኞቹ መኪኖች ውስጥ ያለው የተወሳሰበ ሜካኒካዊ አሠራር (ሞተሩ ፣ ባትሪው ፣ ነዳጁ እና ሌላው ሁሉ) ምን እንደሆነ ስለማያውቁት አላሳሰባቸውም ። መኪናዋ እነሱን ማስገባት እንድትችል አድርገው ፥ በቅርጿ ደግሞ የሚያውቋቸውን መኪኖች እንድትመስል አድርገው ከሠሯት እና መሪ እና የመሳሰሉትን ከላይ የሚታዩ አካላት በቦታ በቦታቸው ካኖሩ በኋላ እንደተሳካላቸው አስበው በነጋታው መኪናዋን ለማንቀሳቀስ ቀጠሮ ያዙ ። መንግሥቱም ዋና መሃንዲስ እንደመሆናቸው የሹፌርነቱን ሚና ወሰዱ ። በዚህ ሥልጣናቸው የተነሣም መኪናዋን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲነዷት ጋቢና ውስጥ ከአጠገባቸው መቀመጥ ከሚፈልግ ልጅ ገንዘብ ተቀብለው ሁሉ ነበር ። ምን ያደርጋል ፥ በነጋታው የክት ልብሳቸውን ለብሰው ፥ በባልንጀሮቻቸው ታጅበው መኪናቸውን ለመንዳት ወደቆመችበት ሲሔዱ ማንነቱ ያልታወቀ ባለጋራ አፈራርሷት ጠበቃቸው ።

የአእላፋት ዝማሬም የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ለመምሰል የሚሞክረው በዚህ መንገድ ነው ። ውስጣዊ

[4] *Didascalia Apostolorum*, ed. Alistair Stewart-Sykes (Brepols Publishers, 2009) Chapter 12, no. 2, p. 176-7 (Mentioned in David Bentley Hart, *Atheist Delusions*, (Yale University Press, 2009), p. 170

አሠራሩ እና አካሔዱ ግን ደጋግሜ እንዳልሁት በዘመናችን ከምናውቃቸው secular ሁነቶች ፥ በተለይም ከኮንሰርቶች የተቀዳ ነው ። ከሚነገረውና ከሚሠራው ሁሉ መገንዘብ እንደሚቻለው ዋናው ጭንቀት የተሳታፊው ብዛት ፣ የቪድዮውና የፎቶዎቹ ጥራትና ውበት ፣ የስክሪኖች መኖር ፣ የልብስ ማማር ፣ የታዋቂ ሰዎች መገኘት ፣ በብዙ ሚዲያዎች የመተላለፉ እና በውጭ ሚዲያዎች የመዘገቡ ነገር ነው ። ይህም በመሆኑ ለዝማሬ የጠሯቸውን ሰዎች ተራ እና ክቡራን ብለው መክፈላቸው እንዴት ከክርስትናና መንፈስ ጋር እንደሚጋጭ አልታያቸውም ።

ይህ ዓይነቱ መረዳት nominalism ይባላል ። ግልብነት ብለን ልንተረጉመው እንችላለን ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረጉትን ነገሮች በሙሉ ከአለባበስ ጀምሮ እስከ ምሥጢራቱ ድረስ ሊኖራቸው ከሚገባው ዋጋ እና ትርጉም የማፋታት ተግባር ነው ። ለምሳሌ የአእላፋት ዝማሬን መላእክትና እረኞች አንድ ላይ መዘመራቸውን የምናስታውስበት የእነርሱን ምስጋና የምንደግምበት ነው የሚል ንግግር ይደረጋል ። ነገር ግን ነገሩ ሲደረግ በመላእክትና በእረኞቹ መካከል ከነበረው ኅብረት የሚቃረን ክፍፍል VIP በተባሉት ሰዎችና በሌላው ሕዝብ መካከል ይሠራል ። ይህን ማድረግ በቅድሚያ ለሁነቱ ሊሰጥ ከተሞከረው ትርጉም ጋር እንዴት እንደሚላተም ልብ የሚል የለም ። መላእክትን ከእረኞች ጋር አንድ ያደረገው በዓል ፥ ቲከቶከሮችን እና ተዋናዮችን "ከሌላው ሕዝብ" ጋር አንድ ማድረግ አይችልም ። (በቤተ ክርስቲያን ዐውድ በደኅንነት ምክንያት ወይም ሌላ መረባበሽን ለማስቀረት ሲባል በወንዶችና በሴቶች መካከል እንደሚደረገው ያለ ክፍፍል ችግር አይኖረውም ። ነግር ግን VIP የሚለው ቃል እንዲያ የተባሉት ሰዎች ከሌላው ምእመን የበለጠ ዋጋ እንዳላቸው ነው የሚናገረው ። ይህ ነው ነገሩ ፈጽሞ ተቀባይነት እንዳይኖረው የሚያደርገው ።)

በዚህኛው ዓመት ደግሞ ከታዋቂ ሰዎች ይልቅ ቆራቢዎች VIP ተብለው የተለየ ቦታ እንዲሰጣቸው መታሰቡ ተሰምቷል ። ማሻሻያ መሆኑ ነው ። አዘጋጆቹ ዋናው ቅሬታ ቦታው ለአርቲስቶች መሰጠቱ ሳይሆን እንዲህ ዓይነት ክፍፍል መፈጠሩ በራሱ እንደሆነ አልተረዱም ። በእርግጥ ከክፍፍሉም በፊት የአእላፋት ዝማሬ የሚለው ሐሳብ እና ሁነት በራሱ ተገቢ አለመሆኑንም አልተረዱም ። VIP ተብሎ ለተወሰኑ ሰዎች ቦታ መሰጠቱም ሆነ ከዚህ ቀጥዬ የማነሣቸው ነገሮች የአእላፋት ዝማሬ ላይ ሊስተካከሉ የሚገቡ ነገሮች አይደሉም ። የአእላፋት ዝማሬ ሥሪት መገለጫዎች ናቸው እንጂ ። የአእላፋት ዝማሬ የሚታረሙ ችግሮች ያሉበት ሁነት አይደለም ። እርሱ ራሱ መታረም ያለበት ችግር ነው እንጂ ።

የዚህ ግልብ መረዳት ሌላኛው መገለጫ በአእላፋት ዝማሬ ላይ የነበረው ስፖንሰርሺፕ ነው ። የአእላፋት ዝማሬ እንደ ማንኛውም ኮንሰርት ስፖንሰሮች ነበሩት ። ስፖንሰሮቹም በሰጡት ገንዘብ መጠን ልዩ ልዩ ደረጃ አላቸው ። ኢጃትም በመግለጫው ስፖንሰር ያደረጉትን ድርጅቶች በየደረጃቸው እየጠቀሰ ዕውቅና ሰጥቷቸዋል ። ኢጃት ልክ ለታዋቂ ሰዎች ከፍ ያለ ቦታ እንደመስጠቱ ሁሉ ይህን ማድረጉም የተገባ እንዳልሆነ አልታየውም ።

ስፖንሰርሺፕ የንግድ ሥራ ነው ። ማለትም ስፖንሰር ተደራጊው ፥ ለምሳሌ አንድ ታዋቂ ሯጭ ወይም ዘፋኝ ፥ ከአንድ ድርጅት ጋር የስፖንሰርሺፕ ስምምነት ሲፈራረም ፥ እሱ ታዋቂነቱን ተጠቅሞ ስፖንሰር አድራጊዎቹን ከአድናቂዎቹ ጋር ሊያስተዋውቃቸው ፥ እነርሱ ደግሞ ለዚህ አገልግሎቱ ገንዘብ ሊከፍሉት የሚደረግ ስምምነት ነው ። በሌላ አነጋገር አልበሙን ወይም ስሙን እየሸጠላቸው ነው ። እንዲሁ ፥ የአእላፋት ዝማሬም ስፖንሰርሺፕን ለመጠቀም ሲፈቅድ ዝማሬውን ሸቀጥ እያደረገ ነው ።

ይህን ስል 'ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በፈቀዱት አቅም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሊሳተፉ አይችሉም ፤ ገንዘባቸውን ለቤተ ክርስቲያን ሊሰጡ አይችሉም' ለማለት አይደለም ። መቻል ብቻ ሳይሆን ሊያደርጉት ይገባል ። ነገር ግን በአጸፌታ በአደባባይ መመስገናቸውን እና መተዋወቃቸውን የሚፈልጉ ከሆነ ነገሩ ከአገልግሎት ቁጥር ወጥቷል ። ይህ ጌታ ፈሪሳውያንን ምጽዋት ስትሰጡ በአደባባይ መለከት ታስነፋላችሁ ብሎ ከወቀሳቸው በምን ይለያል ? እንግዲያውስ እነዚህም ዋጋቸውን ከሰዎች ያገኛሉ ።

ኢጃትም ቢሆን ለአገልግሎት ሲል ከሰዎችና ከድርጅቶች ገንዘብ ቢቀበል አያስነቅፈውም ። ቢያመሰግናቸውም ሰዎቹና ድርጅቶቹ መመስገናቸው በሰማይ ዋጋቸውን እንዳያሳጣቸው እንጂ ከተቀባዩ አንጻር የተገባ ይሆን ነበር ። ነገር ግን ለስጦታው ደረጃ አውጥቶ ከፍ ባለ ደረጃ መመስገን ከፈለጋችሁ ይህን ያህል ፥ ዝቅ ባለ ደረጃ ከፈለጋችሁ ደግሞ ይህን ያህል ክፈሉ ወደ ማለት ከገባ ነገረ ሥራው ከባለ አልበሙ ዘፋኝ ምንም አልተለየም ። እንዲያውም በቤተ ክርስቲያን ስም በመደረጉ ይህኛው

በአጅጉ ይከፋል ። መቅደሱ ውስጥ ካሉት ርግብ ሻጮች የሚለይ አይደለም ።

የኢጃት ሰዎች ግን እንዲህ ያለ ንግድ ውስጥ መሠማራታቸው ሳያንስ ነገረ ሃይማኖትን ለዚህ ንግድ መጠቀሚያ ለማድረግም ፈቅደዋል ። ኢጃት ለስፖንሰሮቹ የሰጣቸውን ደረጃዎች ሲሰይም በሌሎች ሁነቶች እንደምናውቀው የፕላቲነም ፣ የወርቅ ፣ የብር ወዘተ የሚለውን አካሔድ ከመጠቀም ይልቅ "መንፈሳዊ" መንገድን ለመከተል በመምረጥ ፥ ሰብአ ሰገል ለጌታ ያመጡለትን ስጦታዎች አብነት አደረገ ። ከፍ ያለ ገንዘብ የሰጡትን የወርቅ ደረጃ ስፖንሰሮች አላቸው ። ከእነሱ ዝቅ ያለ ገንዘብ የሰጡት የዕጣን ደረጃ ፥ ከእነሱ በታች የሰጡትን ደግሞ የከርቤ ደረጃ ስፖንሰሮች አላቸው ።

የሐሙስ ውዳሴ ማርያም ስለ እነዚህ ሦስት ስጦታዎች እንዲህ ይላል ። "አምጽኡ ዕጣነ ከመ አምላክ ውእቱ ፣ ወርቀ እስመ ንጉሥ ውእቱ ፣ ወከርቤ ዘይትወሃብ ለሞቱ ማኅየዊ ።" (አምላክ ነውና ዕጣን አመጡለት ፤ ንጉሥም ነውና ወርቅን ፤ መድኃኒት ለምትኾን ሞቱም የሚሆን ከርቤን ።) እነዚህ ሦስት ስጦታዎች ሰብአ ሰገል ጌታችንን ልዩ ልዩ የሆነ ክብሩን ሲገልጡ እና በክብሩ ሁሉ ሲያከብሩት ያቀረቡለት እንጂ አንዱ በዋጋ ከሌላው በልጦ ወይም አንሶ የተሰጡ አይደሉም ። እንኳን በዚህ ዓውድ በሌላም ዓውድ ቢሆን የሰዎች ስጦታ በሚያወጣው ዋጋ ልክ አይመዘንም ። ነውር ነው ። ጸያፍ ነው ። ኢጃት እነዚህን ስጦታዎች ደረጃ ሲያወጣላቸው እጅግ የሚያሳፍርና የሚያሸማቅቅ ነገረ ሃይማኖታዊ ጥፋት ነው የፈጸመው ። ይህ ሲሆን ከየትኛውም አቅጣጫ ተቃውሞ አለመነሣቱ ደግሞ የባሰ ያሳፍራል ።

ኢጃት ለስጦታዎቹ ደረጃ የማውጣቱን ነገር በስፖንሰርሺፑ አላበቃም ። ምእመናንም ለደብረ ሮሐ ላሊበላ መባዕ እንዲሰጡ ባደረገው ጥሪ ፥ 'ያላችሁን ስጡ' ማለት ሲችል ፥ መባውን በተሰጠው ብር መጠን የወርቅ ፣ የዕጣን እና የከርቤ ደረጃዎች አወጣለት ። ከአሥር ብር እስከ መቶ ብር የተሰጠ መባዕ 'ከርቤ' ፣ ከመቶ እስከ አንድ ሺህ የተሰጠ 'ዕጣን' ፣ ከሺህ በላይ የተሰጠ ደግሞ 'ወርቅ' ተብለው ደረጃ ተሰጣቸው ። ከላይ እንዳነሣነው የሰብአ ሰገልን ስጦታዎች ማበላለጡ በራሱ ትልቅ ጥፋት ነው ። እነርሱ ግን ከዚህ አልፈው መባዕውንም በተሰጠው ገንዘብ መጠን የሚለካ አደረጉት ። በሌሎች ጉዳዮች ስል እንደነበረው ይህም መንገድ የአእላፋት ዝማሬ የጠረገው አይደለም ። የንግሥ በዓላት ምእመናንን አስጨንቆ ገንዘብ የመቀበያ መድረኮች ከሆኑ ሰነባብተዋል ። ሲሰጥም ምስጋናውና ውዳሴው በተሰጠው ገንዘብ መጠን ከሆነ ውሎ አድሯል ። ለምእመናን ከማስተማራቸው ይልቅ ምእመናንን በማባባት ፣ በማሰልቸት እና አንዳንዴም የማስፈራራት ያህል በማስጨነቅ ገንዘብ የማሰባሰብ ችሎታቸው ታይቶ በየደብሩ የሚጠሩ "መምህራንም" ተፈጥረዋል ። ይህን ነገር ልንዋጋው በተገባን ነበር ። ኢጃት ግን ይህን ተገቢ ያልሆነ ሥራ አጽድቆ ይልቁንም ከክርስትና በተቃረነ የነገረ ሃይማኖት አመክንዮ ሊደግፈው ፈለገ ።

የአእላፋት ዝማሬ መባዎቹን የመደበበትን መንገድ በቅዳሴያችን ወደ ቤተ ክርስቲያን መባዕ ይዘው የሚመጡ ሰዎች ከሚታሰቡበት ጸሎት ጋር ስናነጻጽረው የነገሩ መንፈስ ከሥርዓተ አምልኮው ወደ መቃረን መድረሱን እንመለከታለን ።

> "ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንን እና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን ። ከሁሉ በላይ በምትሆን በከበረች በአንዲት ቤተ ክርስቲያን መባዕ ስለሚያገቡ ፣ መሥዋዕቱን ፣ ቀዳምያቱን ፣ ካሥር አንዱን ፣ የመታሰቢያ ምስጋና ፤ ብዙውን እና ጥቂቱን ፥ የተሰወረውን እና የተገለጸውን ። ይሰጡ ዘንድ ሲወዱ የሚሰጡት ከሌላቸው ላይ ፈቃዳቸውን ተቀብሎ መንግሥተ ሰማያትን ይሰጥ ዘንድ ፤ ለሁሉ በረከትን የሚያድልበት ሥልጣን ገንዘቡ የሚሆን አምላካችን እግዚአብሔር ።"[5]

በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የመባዕ ጸሎቱ የኢጃትን ሐሳቦች ለመቃወም የተጻፈ እስኪመስል ድረስ ነው ። ኢጃት ለሚሰጠው መባዕ እንደብዛቱ መጠን ደረጃ አወጣለት ። በኢጃት ሒሳብ 10 ብር የሰጠ እና 1000 ብር የሰጠ ለየቅል ነው ። ቅዳሴውን ያዘጋጁት አባቶች ግን ብዙውንም ጥቂቱንም ፣ የተሰወረውንም የተገለጸውንም ያለ ልዩነት ያዩዋቸዋል ። ብዙውን እና ጥቂቱን ያሉት በሁለቱ መካከል ልዩነት እና ደረጃ ለማውጣት ሳይሆን ሰጪው ጥቂት ነው ብሎ እንዳይሳቀቅ ነው ። የተሰወረውን እና የተገለጸውን ሲሉም እንዲሁ በኅቡዕ የተሰጠው ስጦታ ከእግዚአብሔር የተሰወረ አለመሆኑን ፣ ካህናቱ እንኳን ሰጪውን አውቀው ስሙን ባይጠሩት ወይ በኅሊናቸው ባያስቡት ከእግዚአብሔር ዋጋውን

[5] *መጽሐፈ ቅዳሴ* ፣ (ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ፣ 2002) ፣ ገጽ 45

እንደማያጣ ሲገልጡ ነው ። ከዚህም አልፈው "ጥቂት" የሆነውን ወይም በሥውር የተሰጠውን ቀርቶ ፥ ሊሰጡ ፈልገው የሚሰጡት ላጡት እንኳን ፍላጎታቸው ብቻ ተቆጥሮ ዋጋ ያገኙበት ዘንድ በመለመን የእግዚአብሔር ሚዛን የመባውን መጠን ሳይሆን የሰውን ፈቃድ እንደሚለካ ያስተምራሉ ። ከልብ ለመስጠት ፈቃድ ይኑር እንጂ መባው አነሰም በዛም ፥ ተሰጠም አልተሰጠም ፥ ዋጋው እኩል ነው - መንግሥተ ሰማያት ። እንደ ኢጃት ከሆነ ግን እንኳን ሊሰጥ ፈልጎ ያጣ ፥ 5 ብር የሰጠ ሰውም ምንም ዋጋ የለውም ። 10 ብር የሰጠውም ከምንም ላይ ይስጠው መቶ ብር ከሰጠው ያነሰ ነው የሰጠው ። መቶ የሰጠውም አንድ ሺህ ብር ከሰጠው ያነሰ ነው የሰጠው ። ሌላው ሁሉ ቢቀር የኢጃት ሰዎች ጌታችን ሁለት ሳንቲም ለቤተ መቅደስ መስጠቷን አይቶ 'ከሁሉ አብልጣ ሰጠች ፥ ያላትን ሁሉ ጥላለችና' ብሎ መበለቲቱን እንዳመሰገናት አላነበቡም ይሆን ?

በዘመናውያን መዝሙሮችና ስብከቶች ፣ እንደ የአእላፋት ዝማሬ ባሉ ሁነቶች እና ሥርዓታዊ በሆነው አምልኮ ይዘት መካከል ሰፊ ገደል ለመኖሩ ይህ ነገር ጥሩ እና በቂ ማሳያ ነው ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለት የተለያዩ ጎሊናዎች መኖራቸው በዚህ ውስጥ በግልጽ ይታያል ። በዚህ የተነሣ ነው እንዲህ ያለ ኢክርስቲያናዊ የሆነ መረዳት በጉልህ ሊነገር እና ሊተገበር የቻለው ። መረዳቱ ደግሞ በኢጃት ወይም በአእላፋት ዝማሬ የተጀመረ ስላልሆነ ፣ አስቀድሞ የዳበረ እና በምእመናን ኅሊና ውስጥ የነበረ ስለሆነም ነው ምንም ዐይነት ተቃውሞና ተግሣፅ ያልተሰማው ።

በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት የተቃረኑ ኅሊናዎች ሊኖሩ ይችላሉ ? እንዲህ ያሉት ሁለት ሚዛኖች በአንድ ቤት አይኖሩምና አንዱን መምረጥ አለብን ። ወይ የወንጌሉን እና የቅዳሴውን ፣ አሊያም የኢጃትን ። 'ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው የለምና' ።

※ ※ ※

በተማሪነት ዘመኔ መጻሕፍትን የማነበው ከዚህም ከዚያም እያልሁ ነበር ። በሬዲዮ ከሰማሁት ፣ አጠገቤ ያለ ሰው ከጠቆመኝ ፣ ቤተ መጻሕፍት ገብቼ ሳይ ዓይኔ የገባውን እና ከፍቼ ስሞክረው የተመቸኝን ወዘተርፈ ። በሒደት የተሻለ መረጃ በኖረኝ እና የንባብ አቅሜ በዳበረ መጠን የማነባቸውን መጻሕፍት በደንብ መምረጥ ቻልሁ ። አሁን ደንበኛ ምርጫ ከኖረኝ በኋላ ወደኋላ ተመልሼ ያኔ በጀማሪነት ዘመኔ ያነበብኳቸውን መጻሕፍት ሳስታውሳቸው ወይም መልሼ አግኝቼ ስመለከታቸው አንዳንዶቹን በማንበቤ በእጅጉ እጸጸታለሁ ። አንዳንዶቹ ደግሞ ምንም እንኳን ክፋት ባይኖርባቸውም እነሱን በማንበብ ያጠፋሁት ጊዜ እንደተቃጠለ ይሰማኛል ።

እርግጥ ነው በመጨረሻ ወደ ደረስሁበት የንባብ ሥፍራ እንድደርስ ያ በዳበሳ እና በጥቆማ የተደረገ ኅሰሳ መደረግ ነበረበት ። ያ ማለት ደግሞ በወቅቱ ከነበርሁበት ደረጃ አንጻር (የሚመራኝ ሰው እስካልነበረ ድረስ) እነዚያን ረብ የለሽ መጻሕፍት ሳላነብ ወደ ጥሩዎቹ መጻሕፍት መድረስ አልችልም ነበር ማለት ነው ። ነገር ግን ወዳለሁብት ደረጃ እንድደርስ ያስቻለኝ ኅሠሣ አካል ስለነበሩ ብቻ እነዚያ ረብ የለሽ መጻሕፍት አሁን ወዳለሁበት እንድደርስ አግዘውኛል ማለት አይደለም ። ይልቁንም ከጥሩዎቹ መጻሕፍት የተነሣ ረብ የለሾቹ መጻሕፍት ወዳለሁበት ከመድረስ ሊገቱኝ አልቻሉም ። ኅሠሣው የግድ እስከሆነ ድረስ እነዚህን መጻሕፍት ያለማንበብ ምርጫ አልነበረኝም እንጂ ለማንበብ ፍላጎቴ እነዚህ መጻሕፍት ተገቢዎቹ አቅርቦቶች አልነበሩም ። እንዲያውም ጥሩዎቹ መጻሕፍት ባያድኑኝ ኖሮ ወደ ጥፋት ሊያደርሱኝ ወይም እስከ መጨረሻው እንደነሱ ያሉ መጻሕፍት ላይ ጊዜዬን ሳቃጥል እንድኖር ፥ አሊያም ማንበብን እርም እንድል ባደረጉኝ ነበር ።

ስለዚህ ዛሬ ሌላ ተማሪ መጥቶ እኔን ምን ማንበብ እንዳለበት ቢጠይቀኝ ፣ በእነዚያ መጻሕፍት በኩል አልፎ እኔ ወደ ደረስሁበት እንዲደርስ አልመክረውም ። እንዲያውም በተቻለኝ መጠን ከነዚያ መጻሕፍት አርቀዋለሁ እንጂ ። አእምሮው ሳይበከል ፣ ጊዜውም ሳይባክን ወደተሻለ የንባብ እና የመረዳት ደረጃ እንዲደርስ ከማውቃቸው መካከል የተሻሉትን መጻሕፍት ብቻ ነው መርጬ የማቀርብለት ።

በአእላፋት ዝማሬ ማግስት ከብዙ ሰዎች ጋር ባደረግኋቸው ውይይቶች ውስጥ በተደጋጋሚ የተነሣ አንድ ነጥብ ነበር ። ይኸውም እነርሱ የሚያውቋቸው ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ጋር እውቂያ ሳይኖራቸው ወይም ያን ያህል ቅርበት ሳይኖራቸው ሳሉ የአእላፋት ዝማሬ ላይ ከተሳተፉ በኋላ ግን ቤተ ክርስቲያን መሔድ ማዘውተር እንደ ጀመሩ ፣ የንስሐ አባት እንደያዙ ፣ ማስቀደስ እንደጀመሩ ወዘተርፈ ነው ። ስለዚህ የአእላፋት ዝማሬ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመቅረቢያ አጋጣሚ ሆኖ አገልግሏል የሚል ነው ዋናው ነጥብ ። ይህ እውነት እንደሆነ እና እኔ የማላውቃቸው እንዲህ ያሉ ብዙ ሰዎች እንደሚኖሩም አልጠራጠርም ። በአእላፋት ዝማሬ በኩል አልፈው ወደ ንሥሐ እና ወደ ቅዳሴ የደረሱ ሰዎች ስላሉ ደስ ይለኛል ።

ነገር ግን እንዲያ የመሆኑ ዕድል ስላለ ብቻ የአእላፋት ዝማሬን መቀበል ወይም ማበረታታት ተገቢ አይሆንም ። ይህ ነጥብ ውሃ ይቋጥር የነበረው የአእላፋት ዝማሬ በባሕርዩ ፣ በአፈጣጠሩ ወደ ቅዳሴ ፣ ወደ ንስሐ የሚመራ በሆነ ነበር ። ነገር ግን እንዲህ እንዳልሆነ ባለፉት የጽሑፌ ክፍሎች አሳይቻለሁ ።

የአእላፋት ዝማሬ ተሳታፊዎቹን በቀጥታ ወደሚገባው ቦታ የሚመራ ስላልሆነ ፥ ምእመናን በአርሱ በኩል ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ አልመክርም ። ልክ እኔ ዕድለኛ ሆኜ አመለጥሁት እንጂ በእነዚያ አይረቤ መጻሕፍት የተነካ ወደ ጥሩዎቹ መጻሕፍት ሳልደርስ የመቅረት ዕድል እንደነበረኝ ሁሉ የአእላፋት ዝማሬንም ለምእመናን እንዲህ ያለ ወጥመድ አድርጌ ነው የማየው ። ከአእላፋት ዝማሬ አልፈው ቅዳሴንና ንስሐን የሕይወታቸው ማዕከል ማድረግ የቻሉ ሰዎች ዕድለኛ ናቸው ። እንጂ የአእላፋት ዝማሬ በራሱ ወደዚያ የሚመራ ነገር አይደለም ። ይልቁንም ሁለት መጻሕፍት - አንዱ ጥሩ ፣ ሌላው ደግሞ ረብ የለሽ ሆነው ሳለ አንድ ሰው ማንበብ ፈልጎ ወደ ቤተ መጻሕፍት በመሔዱ ብቻ ሁለቱንም አንድ መደርደሪያ ላይ አጠገብ ለአጠገብ ተቀምጠው የማግኘት ዕድል እንዳለው ፣ የአእላፋት ዝማሬም ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ እና ከምሥጢራት አጠገብ የሚገኘው በይዘቱ መመሳሰል ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን አፀድ ውስጥ በመገኘቱ ነው ።

በቤተ ክርስቲያን ዓውድ ይህ መከራከሪያ ብዙ ነገሮችን በተመለከተ ሊቀርብ ይችላል ። አንዳንድ ሰዎች ከአላማኝነት በፕሮቴስታንቲዝም በኩል ወደ ክርስትና ይመጣሉ ። ሌሎች "ባሕታዊ" ገብረ መስቀል ፣ "አባ" ዮሐንስ ወይም "መምህር" ግርማ ምክንያት ሆነዋቸው ይመጣሉ ። አንዳንዶች ሰዎች መተት ሠርተውባቸው ለመፈወስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ ። እንዲህ ያሉ አጋጣሚዎች ስላሉ ብቻ ግን እነዚህን ነገሮች መልካም ናቸው አንልም ።

ይልቁንም አንድ ሰው ፕሮቴስታንታዊ የሆነ ሥሪቱን እንደያዘ ወደ ቤተ ክርስቲያን ቢመጣ ሥሪቱ ኦርቶዶክሳዊውን እውነታ እንዳይረዳ እንቅፋት ስለሚሆንበት ያን ማስጣል እንደሚገባ ፥ እኔም ከአእላፋት ዝማሬ በተገኘ ሥሪት ወደ ቅዳሴ እና ንሥሐ የሚመጡ ሰዎች ራሳቸውን መፈተሽ ይገባቸዋል ብዬ ነው የማስበው ።

ይህ ደግሞ ሥጋት ብቻ ሳይሆን ተገልጦ የሚታይ ችግር ነው ። ማኅሌቶቻችን ከጸሎት ይልቅ የድምቀት ዐውድ ተደርገው መታየት መጀመራቸውን ከላይ አንሥቻለሁ ። ይህ ከዐውደ ምሕረት ጉባኤዎች የተጋባ ካልሆነ ከወዴት መጣ ? በየደብራቱ ትልልቅ ሕንፃዎች ለመገንባት የሚደረገውን ሩጫ እና ፉክክርም መታዘብ ይቻላል ። በንግሥ በዓላት ላይ ለመድረክና ለዲኮር የሚደረጉ ወጪዎች ለዚህ ምስክሮች ናቸው ።

እርግጥ ነው ፣ ካለን ነገር መካከል የተሻለውን ለእግዚአብሔር ቤት መስጠት ይገባናል ። ነገር ግን ከላይ እንዳልሁት ዋናውን ቁም ነገር ትተን አፍአዊው ነገር ላይ ካተኮርን መስጠታችን ምን ዋጋ አለው ? እነዚህ ትልልቅ ሕንፃዎች ቅዳሴ ተድፋፍቶ የሚቀደስባቸው ከሆኑ ምን ዋጋ አላቸው ? የተጌጡት መድረኮች የንግድ ቦታ ከሆኑ ምን ዋጋ አላቸው ? እንዲህ ያለው አፍአዊ ነገሮች ላይ ያተኮሩ እና ድምቀትን ማዕከል ያደረጉ አሠራሮች የአእላፋት ዝማሬ ላይ ከምንታዘበው አመለካከት ጋር ተመሳሳይ ነው ።

ከጥቂት ወራት በፊት በሶሻል ሚዲያ ተጠራርተውና ተመራርጠው ለመቁረብ ቀጠሮ የያዙት ሰዎችም የዚህ አካሔድ ሌላ ምሳሌ ናቸው ።

አብዛኛው ምእመን በየሳምንቱ ቅዳሴ ላይ እየተገኘም እንኳን ከምሥጢር ርቆ መኖሩ ትክክል አለመሆኑ የታመነ ነው ። አሁን አሁን ይህ ልማድ መቅረት እንዳለበትና ምእመናን ሁሉ ንስሐ ገብተው ሥጋ ወደሙን መቀበል እንዳለባቸው ከየአቅጣጫው ተግሣፅ እና ማሳሰቢያ ይደመጣል ። ማሳሰቢያውና ተግሣፁ ትክክል ነው ። ነገር ግን ይህን ለውጥ ለማምጣት እየተሔደባቸው ያሉት መንገዶች አስደንጋጭ ናቸው ።

በፊት ሰዎች አንድ ሰው 'ቆረበ' ከተባለ እንደ መነኮሰ ወይም ሊሞት እንደተቃረበ አድርገው ነበር የሚመለከቱት ። አሁንም እንዲያ የሚያስቡ ብዙዎች አሉ ። ከምሥጢር ለመሳተፍ ፍጽምና ላይ መድረስ ፣ ወይም ቢያንስ ከዓለም ፈጽሞ መለየት አስፈላጊ ነው ብለው ያስቡ ነበር ። ስለዚህም እድሜያቸው በጣም ገፍቶ ፣ ወይም ጽኑ ሕመም አጋጥሟቸው ለሞት የተቃረቡ ካልመሰላቸው በስተቀር ወደ ሥጋ ወደሙ ለመቅረብ አይደፍሩም ። እንዲያውም ከዚያ በፊት መቁረብ ትክክል አይደለም ብለው ያስባሉ ። ይኽ መታረም ያለበት አሳብ ነው።

አሁን አሁን ደግሞ ከምሥጢር መሳተፍን በተመለከተ አዳዲስ መረዳቶችን እና አቀራረቦችን እያየን ነው ።

ከወራት በፊት በሶሻል ሚዲያ ተጠራርተውና ተመራርጠው ለመቁረብ ቀጠሮ የያዙት ሰዎች የዚህ ዐዲስ መረዳት ጥሩ ማሳያ ናቸው ። እነዚህ ሰዎች ምስጢር መሳተፍን ለሞት እንደመቅረብ እንደማያዩት ግልጽ ነው ። ነገር ግን እይታቸው ከዚያ የሚብስ እንጂ የሚሻል አይደለም ።

እነዚህ ሰዎች ምሥጢር ለመሳተፍ የተነሡት አንዳች በማኅበራዊ ሚዲያ የሚተዋወቅን ሁነት ለመካፈል እንደሚነሣ ነው ። አንድ ሰው ከምሥጢር መሳተፍን በተመለከተ ሊያስተምር ይችላል ። ከዚያ በኋላ ግን በዚህም ሆነ በሌላ አጋጣሚ ርቆ የነበረ እና ወደ ምሥጢር መመለስ የፈለገ ሰው ባለበት ቦታ በንስሐ አባቱ እየተመራ እና እየተመከረ ይህን ለማድረግ ይጥራል እንጂ በማኅበራዊ ሚዲያ ከሚያውቀው ሰው ጋር አብሬ ምሥጢር ልሳተፍ ብሎ ቀጠሮ ለምን ይይዛል ? ቁም ነገሩ ምስጢር ከመሳተፉ ሳይሆን ከዚያ ሰው ጋራ መሳተፉ መሆኑ ነው ። እነዚህ ሰዎች celebrity culture የሚባለውን ፣ ታዋቂ ሰዎችን ተከትሎ የመልበስ ፣ የመመገብ ፣ ሁነት የመሳተፍ ወዘተርፈ ልማድ ነው ምስጢር ወደ መሳተፍ ያመጡት ። ‘ከእኛ ጋር ቁረቡ’ ባዮቹም ከእኛ ጋር መቁረብ የሚፈልግ ብለው ከሰው ማመልከቻ ሲቀበሉ እና ሲመርጡ ምሥጢር በመሳተፍ ሰበብ ራሳቸውን ማዕከል ያደረገ ‘Exclusive event’ እያከናወኑ ነው ።

ማስቀደስን እና መቁረብን ከዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር የተቆራኘ እና ሕይወትን የሚቃኝ ሳይሆን የሶሻል ሚዲያ ሱታፌ እና ግብዐት እንዲሆን ሆኗል ።

እነዚህ ተጠራርተው ለመቁረብ የሔዱትም ሆኑ ሌሎች ሰዎች ምሥጢር ለመቀበል የመሔዳቸውን እና የመምጣታቸውን ሒደት በቲክቶክ ፣ በኢንስታግራም እና በሌሎችም ማኅበራዊ ሚዲያ ማሰራጨታቸውም የተለመደ ሆኗል ። በማኅበራዊ ሚዲያ የሚደረግ ነገር ሁሉ ሰው እንዲያየው ብቻ እንጂ ሌላ ምክንያት የለውም ። እነዚህ ሰዎች ምሥጢር ለመሳተፍ በማኅበራዊ ሚዲያ መጠራራታቸውም ሆነ ሒደቱን ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ መለጠፋቸው ከክርስትና ጋር በቀጥታ የሚላተም መሆኑ እንዴት ላይታያቸው ይችላል ?

እንዲህ ያለው የሚታይ መጣረስ ክርስትናን በጠቅላላው ክርስትናን በተለይ ደግሞ ሱታፌ ምሥጢርን በተመለከተ እጅግ ስሑት መረዳት በመካከላችን እንደሰፈነ ያሳያል ።

ሱታፌ ምሥጢርን በተመለከተ የደረስንበት ይህ ስሑት መረዳት በድንገት የመጣ ሳይሆን በሒደት የዳበረ ነው ። ባለፉት ዓመታት በግቢ ጉባኤያትና በሰንበት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሰዎች ንስሐ መግባታቸው እና ከምሥጢር መሳተፋቸው አስፈላጊ መሆኑ ፣ ለውጥ ተብሎ የሚቆጠረውም እንዲህ ያለ ለውጥ መሆኑ ስለታመነበት ፥ እነዚህ ነገሮች በእቅድ መሠራት ጀምረዋል ። ይህን ያህል ሰዎች ንስሐ ማስገባት ፣ ይህን ያህል ሰዎች ወደ ምስጢር እንዲቀርቡ ማድረግ ወዘተርፈ ። እንዲህ ያሉት እቅዶች ንሥሐ እና ሱታፌ ምሥጢር ለድኅነት ያላቸውን ፋይዳ ልክ የልደት ካርድ ማውጣት ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ካለው ፋይዳ ጋር ተመሳሳይ አድርጎ ከመረዳት የመነጩ ናቸው ።

በዘመናዊው የሥራ ቦታ ሠራተኞች ከሥራ ሲገቡ እና ሲወጡ ወረቀት ላይ የሚፈርሙት ፊርማ ሥራቸውን ለመሥራታቸው ማረጋገጫ ተደርጎ ይወሰዳል ። ነገር ግን አንድ ሠራተኛ ምንም እንኳን ወረቀቱ በሰዓቱ ገብቶ በሰዓቱ መውጣቱን ቢያሳይም እዚያ በሚቆይበት ጊዜ የራሱንም ሥራ የማይሠራ ፣ ሌሎችንም እንዳይሠሩ የሚያደርግ ፣ ደንበኛ ወይም ባለጉዳይ የሚያጉላላ ይሆናል ። ነገር ግን ወረቀቱን ለተመለከተ ሰው በጊዜ ገብቶ በጊዜ ስለወጣ ብቻ ጥሩ ሠራተኛ ይመስላል ።

የምር ጥሩ ሠራተኛ መሆን በሰዓት መግባትን እና መውጣትን ብቻ ሳይሆን በመግባትና በመውጣት መካከል ብዙ ድካምን እንደሚፈልግ ሁሉ ክርስትናም “በብዙ መከራ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት” የሚደረግ ጉዞ ነው ። አሁን ያዳበርነው መረዳት ግን መከራውን እና ድካሙን ትተን ምሥጢራትን እንደ አቴንዳንስ ተጠቅመን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንደምንችል ነው ።

ስለንሥሐ እና ስለ ሱታፌ ምሥጢር እንዲህ ያለ ሕይወት የተለየው መረዳት ስለዳበረ ነው አሁን የምናየው ዐይነት የታይታ እና የዘመቻ ሱታፌ ሊኖር የቻለው ። ንስሐን እንደ ሕይወት መንገድ ለውጥ ሳይሆን በየጊዜው እንደሚቀርብ ሪፖርት ፣ ሱታፌንም እንደ መሟላት እንዳለበት አንድ ሁኔታ (mere formality) መመልከት ስለተጀመረ በእነዚህ ነገሮች አማካይነት ሕይወትን የመለወጥ ሳይሆን ያለን ሕይወት ላይ አንድ ተጨማሪ ሁነት አድርገን ለመጨመር እንደፍራለን ። ለውጥ እንኳን ቢያስከትሉ አፍአዊ ብቻ ይሆናል ።

ማኅበራዊ ሚዲያ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው ። ማኅበራዊ ሚዲያ በተለያዩ ቅርጾቹ የሕይወታችን ትልቅ አካል እየሆነ መጥቷል ። ምንም እንኳን ማኅበራዊ ሚዲያን በተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ማዋል ቢቻልም ፣ ይዞ የመጣቸው ብዙ ጣጣዎች መኖራቸው ሊካድ አይችልም ። በቅድሚያ ፣ ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ብዙዎች መታየትን ፣ ዝናን ሽተው መገኘታቸው ይታወቃል ። እነዚህ ፍላጎቶች አንድ ክርስቲያን ከራሱ ሊያርቃቸው የሚገቡት ናቸው ። በተጨማሪም ፥ ማኅበራዊ ሚዲያ ሰውን የማጥመድ እና ብዙ ሰዓትን ከቀናችን ላይ የመስረቅ አመል ያለው መሆኑ የተሰወረ አይደለም ። ይህን በማድረጉ ደግሞ በአንድ በኩል ፥ ምንም እንኳን ማኅበራዊ የሚል ቅጽል ቢሰጠውም ፣ ማኅበራዊ ሚዲያ ቤተሰብንም ሆነ ወዳጆችን የማራራቅ ሚና እየተጫወተ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ሐሳባችንን ሰብስበን ቁም ነገር ከመሥራት ይልቅ የመረጥነውን ሳይሆን ያለንበት ማኅበራዊ ሚዲያ የሚያቀርብልንን ይዘቶች በመመልከት ጊዜያችንን እናጠፋለን ።

ታዲያ ሕይወታችንን ክርስቲያናዊ ለማድረግ ስናቅድ እና ስንሞክር ዐቢይ ጉዳይ ልናደርገው ከሚገባን ነገሮች አንዱ እንዲህ ያሉትን የማኅበራዊ ሚዲያ ጉዳቶች እንዴት መከላከል እንደምንችል ነው ። ከማኅበራዊ ሚዲያ ፈጽመን መቆጠብ ባንችል ወይም ይህን ማድረግ የግድ ባይሆንብን እንኳን ፥ ያለንን ሱታፌ የተመጠነ እና ጤናማ ፥ አንዳች ግብ ያለው ለማድረግ መጣር ይኖርብናል ።

ከላይ ያነሣሁትን ምሳሌ ጨምሮ አሁን የምናያቸው አካሔዶች ግን ማኅበራዊ ሚዲያ በሥሪቱ ጭምር ከክርስትና የሚቃረን መሆኑን ልብ የማይሉ ናቸው ። ስለዚህም ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ያላቸውን ሱታፌ ለክርስትና የማስገዛት ሙከራ ማድረግ እንዳለባቸው አይሰማቸውም ። ይልቁንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖራቸውን ሱታፌ የማኅበራዊ ሚዲያ ግብዓት በማድረግ ብቻ ሕይወታቸውን የበለጠ ክርስቲያናዊ ያደረጉ የሚመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ ። ይህን በማድረግ የማኅበራዊ ሚዲያ ሕይወታቸውን ለክርስትናቸው በማስገዛት ፋንታ በቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ሱታፌ የማኅበራዊ ሚዲያ ግብዓት በማድረግ ዋጋ ያሳጡታል ።

አንዲት ሴት ቀድሞ ቲክቶክ ወይም ኢንስታግራም ላይ ሰውነቷን የሚያጋልጥ ልብስ ለብሳ በመዝፈን ተመልካች ለማግኘት ትሞክር ከነበረና ፥ አሁን ግን አካሔዷን በመለወጥ የሀገር ልብስ ለብሳ መዝሙር በመዘመር ያንኑ ግብ ለማሳካት ብትሞክር የቲክቶክን እና የኢንስታግራምን ጾር አሸንፋዋለች ማለት ይቻላል ? በምኩራብ እና በመንገድ መዓዝን ቆሞ መጸለይ ዋጋ የሚያሳጣ ከሆነ ቲክቶክ ላይ መጸለይ እንዴት የተሻለ ሊሆን ይችላል ?

የአደባባይ በዓላት ፣ የንግሥ በዓላት እንዲሁም ማኅሌት ላይ ጭምር ስልኮችና ካሜራዎች የሚጫወቱት ሚና ትልቅ ሆኗል ። በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን ዓውዶች ቅዳሴን ጨምሮ የታይታ ዓውዶች እንዲሆኑ ሆኗል ። የታይታ ፈተና መቼም ቢሆን ሊቀር አለመቻሉ አይዘነጋንም ። እዚህ ጋ ያለው ችግር ግን ፈተናው መኖሩ ሳይሆን ጨርሶ እንደ ፈተና አለመታየቱ ነው ። እንደፈተና እስካየነው ድረስ መፍትሔ እንፈልግለታለን ፣ እንደ ተገቢ ነገር ካየነው ግን ለምን እናርመዋለን ፣ ለምን እንታገለዋለን ?

ልክ የአእላፋት ዝማሬ ኮንሰርት ሂያጆችን ሲጠራ በዘፈን ፋንታ መዝሙር መተካት እንጂ ጠቅላላ መንፈሱ ኮንሰርትን እንደሚከተለው ፣ ይህኛውም አካሔድ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ርቀው ሳሉ ሕይወታቸውን ይገዛ የነበረውን መንፈስ ይዘው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ ነው የሚያደርጋቸው ። ለዚህም ነው ብዙ ሰዎች በአእላፋት ዝማሬ አማካይነት ወደ ንሥሐ እና ወደ ምሥጢር ቢመጡ ራሱ የአእላፋት ዝማሬን ሥሪት እንደያዙ ከሆነ ዋጋ የለውም የምለው ።

※ ※ ※

ሌላው ብዙ ሰዎች ያነሡልኝ ነጥብ ፥ የአእላፋት ዝማሬን ያዘጋጁትም ሆኑ የተሳተፉበት ሰዎች ቤተክርስቲያንን ለመጥቀም እና ወደ እርሷ ለመቅረብ እንጂ ሊጎዷት አስበው እንዳልሆነ ነው ። ይህ ነጥብ ለተዋሥኦዋችን ምንም ጥቅም የለውም ። የእኔ ጉዳይ ከሰዎቹ ፍላጎት አይደለም ።

እንኳን እንዲህ ብዙ ሰው በተሳተፈበት ሁነት ፥ የአንድን ሰው ብቻ እንኳን ውስጣዊ ሐሳብ እና ፍላጎት እንዲህ ነው ለማለት ብዙ ጊዜ አይቻልም ። የራሴን ውስጣዊ ሐሳብ እና ፍላጎት ሳይቀር ብዙ ጊዜ እጠራጠራለሁ ፤ ሰው ራሱን ሳይቀር የመዋሸት ብቃት አለውና ። ነገር ግን ለአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆችም ሆነ ለተሳታፊዎቹ ሐሳባቸውና ፍላጎታቸው ቤተ ክርስቲያንን ለመጥቀምና ወደ እርሷ ለመቅረብ እንደሆነ በድፍኑ እቀበላለሁ ፥ የሚያጠራጥረኝ ሌላ ምክንያት እስካላገኘሁ ድረስ ። መርሳት የሌለብን ፥ ጸሎታችን “አቤቱ አንተን ብንበድል ፥ በማወቅ ፣ ወይም ባለማወቅ ፣ በተንኮልም ቢሆን ፣ በልቡና ክፋትም ቢሆን

. . . በዕውቀት ማነስም ቢሆን . . .'' እንደሚል ፥ ጥፋት በማወቅ ፣ በተንኮል እና በልቡና ክፋት ብቻ እንደማይሠራ ነው ። ጥሩ ያደረግን መስሎን የምናጠፋባቸው ጊዜያት አሉ ።

ጓያ በልቶ ወተት መጠጣት ሽባ ያደርጋል ይባላል ። ሐኪም የሆኑ ሰዎችም ጭምር ይህን አረጋግጠውልኛል ። እንግዲህ ይህን ሳውቅ በሆነ አጋጣሚ አንዲት ሴት ለተራበ ሰው 'ቤት ያፈራውን' ብላ ጓያና ወተት ስታቀርብለት ብመለከት ሴቲቱ ይህን ያደረገችው ለሰውየው በማዘኗ ስለሆነ ብቻ ሰውየው የቀረበለትን እንዲበላ እፈቅዳለሁ ? ለተራበው ሰውና ለሴቲቱ 'ይህ ነገር ሽባ ያደርጋል ይባላል ፣ አንተም ተው አትብላ ፣ አንቺም ሁለተኛ ተሳስተሽ ይህን ምግብ ለሰውም እንዳታቀርቢ ፣ ለራስሽም እንዳትበዪ' ስላቸው ፣ ሴቲቱን ሰውየውን ሽባ ለማድረግ በመሞከር እየከሰስኳት ነው ? የተራበውንስ ሰው 'አልራበህም ፣ ምግብ መብላት አያስፈልግህም' እያልሁት ነው ?

በተመሳሳይ የአእላፋት ዝማሬ ቤተ ክርስቲያንን የሚጎዳት እንጂ የሚጠቅማት አይደለም ስልም ፥ ያዘጋጁትና የተሳተፉበት ሰዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ለመጉዳት የተነሡ ናቸው እያልሁ አይደለም ። ቤተ ክርስቲያንም ልጆቿን ለማጽናትና በስተውጭ ያሉትን ለመጥራት ፣ ዘመኑን ለመዋጀት ሥራ መሥራት የለባትም እያልሁ አይደለም ። መንገዱ ግን ይህ አሁን የታሰበውና የተጀመረው አይደለም እያልሁ ነው ።

※ ※ ※

ባለፉት መቶ ዓመታት ውስጥ ከተፈጠሩት ትልልቅ ለውጦች መካከል በስም ኦርቶዶክስ የሆነ ፥ በልጅነት የጥምቀትን ጸጋ ያገኘ ፥ ነገር ግን በዕለት ተዕለት ሕይወቱ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ቁርኝት የሌለው ሰፊ የማኅበረ ሰብእ ክፍል መፈጠሩ ነው ። ከዚያ በፊት ምንም እንኳን አብዛኛው የማኅበረሰቡ ክፍል ፊደል ያልቆጠረ እና የዳበረ የነገረ ሃይማኖት ዕውቀት የሌለው ቢሆንም (ምናልባትም የደብሩ ቤተ ክርስቲያን የተሰየመለትን ጻድቅ ፣ ሰማዕት ወይም መልአክ ፈጣሪው አድርጎ ሊያስብ እስኪችል ድረስ) ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን የማኅበሩ ማዕከል እንደመሆኗ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ያልተቋረጠ ሱታፌ ማድረጉ አይቀርም ነበር ።

ባለፉት መቶ ዓመታት ግን በተለይ በከተሞች ውስጥ ከኦርቶዶክሳውያን ወላጆች ተገኝቶ ነገር ግን ክርስትና ከመነሣት ባለፈ ይህ ነው የሚባል ሱታፌ ሳይኖረው የሚያድግ እና ከፍ ባለ ቁጥር ከቤተ ክርስቲያን ጨርሶ የሚርቀው ሰው ብዙ ነው ። እኔ ራሴ እንዲህ ካሉት ሰዎች መካከል ነኝ ። በልጅነቴ በየሳምንቱም ባይሆን እሑድ እሑድ ቤተ ክርስቲያን እወሰድ የነበረ ቢሆንም ከፍ ባልሁ ቁጥር ግን ይህም እየቀረ ሔዶ በመጨረሻ በቤተ ክርስቲያን በሚካሔደው ሥርዓተ አምልኮ ያለኝ ሱታፌ ምንም እስኪሆን ደረሰ ። ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ሳለሁ አንድ ጓደኛዬ ስለ ሃይማኖት ጸሎት ሲጠይቀኝ ምን እንደሆነ አላወቅሁም ነበር ። ያም ሆኖ ራሴን ኦርቶዶክስ ነኝ ብዬ ነበር የምገልጠው ። የኦርቶዶክሳዊነቴ መገለጫዎች ደግሞ አንገቴ ላይ ያለው ክር ፣ ሁሉንም ባይሆንም አንዳንዶቹን አጽዋማት መጾሜ እና ፤ አንዳንዴ የማዳምጣቸው መዝሙሮችና ስብከቶች ነበሩ ። ከዚያ በኋላም መልሼ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመቅረብ በመፈለግ በአንድ ወይም በሌላ አጋጣሚ ሥርዓተ አምልኮ ላይ በተገኘሁባቸው ጊዜያት እንደ ልጅነቴ ሁሉ ምን እየተከናወነ እንደሆነ መረዳት አስቸጋሪ ይሆንብኝ ነበር ።

ይህን ርቀት ለማጥበብ ከረዱኝ ነገሮች መካከል ዋናው የቅዳሴው ጸሎት በአማርኛ በሚገባ ሲነበብ ማዳመጥ መቻሌ ነበር ። የቅዳሴውን ይዘት የተሻለ እየተረዳሁ በመጣሁ ቁጥር በዳበሳ ከመቧጠጥ አልፌ የሚጨበጥ እና የጸና ነገር መያዜ ታወቀኝ ። ዐዲስ ዓለም ነበር የተከፈተልኝ ። ከዚያ በፊት ራሴን ለመግራትም ሆነ ስለ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለማወቅ ያደመጥኳቸው መዝሙሮችና ስብከቶች ነበሩ ። ነገር ግን ከቅዳሴው ያገኘሁትን ይዘት እና ውበት ከእነርሱ አላገኘሁም ነበር ።

ስለ የአእላፋት ዝማሬ በተለይ ፣ በጠቅላላው ደግሞ ስለ ዘመናችን ዝማሬዎችና ስብከቶች ጠንካራ አቋም እንድይዝ የሚያደርገኝም ይህ ነው ። ለበሽታችሁ ፍቱን ያልሆነ መድኃኒት ስትቅሙ ከርማችሁ ፣ በመጨረሻ ደንበኛውን መድኃኒት ስታገኙ እና ወዲያው ሲሻላችሁ የፊተኛውን "መድኃኒት" በመውሰድ ስላጠፋችሁት ጊዜ መቆጨታችሁ ይቀራል ? ተመሳሳይ ሕማም ለገጠመው ሰው ሁሉ እየዞራችሁ የኋለኛውን እንጂ የፊተኛውን መድኃኒት እንዳይወስዱ ለመናገር መሻታችሁ ይቀራል ?

ዛሬም ቢሆን ብዙዎች ከቤተ ክርስቲያን ርቀው መኖራቸው በገሃድ የሚታይ እውነታ ነው ። ጊዜ በሔደ ቁጥር ነገሩ እየከፋ እንጂ እየተሻለ እንዲሔድ የሚያደርግ ሥራ አልሠራንም ። ከዚህ አዘቅት ለመውጣት ፥ ለራቁትም ሆነ ለቀረቡት ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን

እውነተኛ መልክ ማሳየት ነው ያለብን ። አሁን የቤተ ክርስቲያን መገለጫ ሆነው በስፋት የሚታወቁት መዝሙሮችና ስብከቶች ግን ልክ የዘመናችን ሴቶች የተዋቡ መስሏቸው ፊታቸውን ከሚያበላሹባቸው ሜክ አፕ እና ሌሎች ሐሳዊ “የመዋቢያ” መንገዶች ጋር ተመሳሳይ ሆነው ነው የሚታዩኝ ። ከሞላ ጎደል የቤተ ክርስቲያንን እውነተኛ ፣ ውብ መልክ የመደበቅ እና የማበላሸት ሚና ነው ያላቸው ።

ከቤተ ክርስቲያን የጠፉትን ለመመለስም ሆነ ያሉትን ለማጽናት ብቸኛውና አማራጭ የሌለው መንገድ ሥርዓተ አምልኮው ነው ። ሕዝቡን እንዴት ወደ ሥርዓተ አምልኮው ማቅረብ ይቻላል ስለሚለው ጥያቄ ያለማቋረጥ ማሰብ እና መጨነቅ ይፈልጋል ። ለእኔ እንደሚታየኝ ቢያንስ ሁለት ዋና ዋና መንገዶች ያሉ ይመስለኛል ። የመጀመሪያው አስቀድሞ የተጀመረውን ሕዝብ ወደ ሚረዳው ቋንቋ የሥርዓተ አምልኮውን ይዘት የመተርጎም ሒደት መቀጠል እና ትርጉሞቹም ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው ። ሰው ለቅዳሴ ወይም ለኪዳን ወይም ለሌላ አገልግሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ ጸሎቱን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እንዲሰማ መሆን አለበት ። ይህ እንዲሆን ደግሞ ካህናት ያለ ጥድፊያ ሥራቸውን ማከናወን ይኖርባቸዋል ። ይህም ብቻ ሳይሆን አገልግሎቶቹ ሰው መገኘት በሚችልበት ሰዓት መካሔድ አለባቸው ። ለምሳሌ አዲስ አበባ ውስጥ ወይም በሌሎች ከተሞችም ቢሆን በተለይ ቅዳሜ እና እሑድ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት በፊት ቅዳሴ መጀመር የለበትም ። ከቅዳሴ በኋላም ምንም መርሐ ግብር መኖር የለበትም ።

ሁለተኛው መንገድ ደግሞ መተርጎም የማይችለውን የቅዳሴን ይዘት ሕዝቡ እንዲረዳው ማስቻል ነው ። የእኛ ሥርዓተ አምልኮ በዋናነት በግዕዝ ነው የሚካሔደው ። ዜማውም የተሠራው ለግዕዙ ንባብ ነው ። ይህን ዜማ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መውሰድ አይቻል ይሆናል ። ለየቋንቋው ዜማ መድረስ ደግሞ (የሚቻል ቢሆንም) በጣም አስቸጋሪ ነው ። ስለዚህ ክርስቲያኖች በተቻለ መጠን ግዕዝ እንዲያውቁ እና የተወሰነም ቢሆን የዜማ ዕውቀት እንዲኖራቸው መሥራት ያስፈልጋል ። ዘመናችን ሕፃናት መላ ዘመናቸውን በትምህርት የሚያሳልፉበት ነው ። ካሰብንበት ሥርዓተ አምልኮውን ለመረዳት የሚያስችላቸው መሠረታዊ ዕውቀት ማስጨበጥ ያን ያህል አስቸጋሪ አይሆንም ።

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የሥርዓተ አልምኮውን በሰፊው ማጥናት እና ነገረ ሃይማኖታችንን እና አገልግሎቶቻችንን ፣ ሕይወታችንን ሁሉ ከሥርዓተ አምልኮው ጋር መስፋትም አስፈላጊ ነው ። ይህን ለማድረግ ደግሞ የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ቤቶች ያስፈልጉናል ። እነዚህም አሁን ያሉትን ጉባኤዎች ያገለሉ ሳይሆኑ እነሱን አካተው በእኛ ጉባኤ የሌሉትን የአባቶች ትምህርቶችና ሌሎችም ጠቃሚ ዕውቀቶች የጨመሩ መሆን አለባቸው ። የዘመናችንን ሰዎችም ሰማዕያን ማድረግ አለባቸው ። እነዚህን በማድረግ በሥርዓተ አምልኮውና በሕዝቡ መካከል ድልድይ መሥራት ይቻላል ብዬ አምናለሁ ።

ሥርዓተ አምልኮውን በሚገባ ስናውቀው እንደ ክርስቲያን ኅብረት ልንከተለው የሚገባውን አነዋወር ፥ በወንጌል የምናገኛቸውን ትእዛዛት እንዴት መተግበር እንደሚገባን እንረዳለን ። ነገር ግን አሁን ቅዳሴውን በዋናነት በዚህ መንገድ እያየነው ስላልሆነ በተግባር የምንኖርበት መንገድ ከቅዳሴው ይዘት በእጅጉ የራቀ ነው ። ቅድም ያነሣሁት በቅዳሴው የመባዕ ጸሎት እና በአእላፋት ዝማሬም ሆነ በየዓውደ ምሕረቱ በምናያቸው ገንዘብ የማሰባሰብ ተግባሮች መካከል የምናየው መቃረን ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው ።

ሌላ ምሳሌ ለመጨመር ያህል ደግሞ የምጽዋትን ነገር ማንሣት ይቻላል ። በቅዳሴው መካከል የሚደረገው ጸሎተ ቡራኬ “በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ በመንበርህ ፊት ምጽዋት ያመጡትንም ተቀበላቸው ።” ይላል ። በዚህ ጸሎት መሠረት ፥ ምጽዋት በዋናነት በሰጪና በተቀባይ መካከል የሚደረግ አይደለም ። ይልቁንም ከሁሉም ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣ እና ከቤተ ክርስቲያን በማኅበሩ ውስጥ እና ከማኅበሩም ውጪ ላሉ ለተቸገሩ ሰዎች የሚሰጥ ነው ። “ሙዳየ ምጽዋት” የሚለውም ቃል የዚሁ እውነታ ምስክር ነው ። ዮስጢኖስ የሚባለው በሁለተኛው ምዕት ዓመት የኖረ የቤተ ክርስቲያን አባት በዘመኑ ለነበረው ንጉሥ በላከው የዕቅበተ እምነት ጽሑፉ ይህን እውነታ ይመሰክራል ።

> “(ለቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን ከሚገኙት ክርስቲያኖች መካከል) ያላቸው እና የፈቀዱት ካላቸው ላይ የወደዱትን ያህል ይሰጣሉ ። ከእነርሱ የተሰበሰበው በጳጳሱ ዘንድ ይከማቻል ። እርሱም መበለቶቹን እና እጓለ ማውታዎቹን ፣ በሕመምና በሌሎችም ምክንያቶች የተቸገሩትን ፣ በዕዳ እና በአገዛዝ የተያዙትን እና በእኛ ዘንድ በእንግድነት የተቀመጡትንም ሁሉ ሰብስቦ

ለእያንዳንዱ እንደሚያስፈልገው ያከፋፍላቸዋል ።”[6]

ይህ ከጥንት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን መገለጫ የሆነ እውነታ በእኛ ዘንድ ግን ተረስቷል ። ሌላው ቀርቶ ሌሎቻችን ከየቤታችን መጥተን ወደ ውስጥ ስንገባ በቤተ ክርስቲያን ደጅ የሚቀመጡት የኔ ብጤዎች በውጭ መቅረታቸው ምን ያህል ከክርስትና መንፈስ የተቃረነ መሆኑን ልብ አንለውም ። የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችም ይህን ተግባር የራሳቸው ኃላፊነት አድርገው አይመለከቱትም ። ሥርዓተ አምልኮአችን ከእለት ተእለት ሕይወታችን ባይነጠል ኖሮ ወደዚህ ዝቅታ ባልደረስን ነበር ።

ስለዚህም ሕዝቡ ሥርዓተ አምልኮውን እንዲረዳ መሆኑ እና ሥርዓተ አምልኮው በጥልቀት መጠናቱ ሁሉንም ለማወቅ ከመጓጓት የሚደረግ አይደለም ። ይልቁንም ሥርዓተ አምልኮውን የነገረ ሃይማኖት እና ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መርሕ ምንጭ ወደ መሆን መመለስ እንችል ዘንድ አስፈላጊ ነው ። በቀደሙት አባቶቻችን “በመንገዳቸው እንሔድ ዘንድ ፣ ፍለጋቸውንም እንከተል ዘንድ ፣ ሁልጊዜውም እነሱን እንመስል ዘንድ ፣ በፍቅራቸውም እንጸና ዘንድ ፣ ባማረ አምልኮ በድካማቸው ከእነርሱ ጋር እንድንታደል” የሚያስችለን መንገድ ይህ ነው ።

በዘመናችን መዝሙርና ስብከት የተሰጣቸው አላስፈላጊ ትኩረት ግን ከዚህ በተቃራኒ በምእመኑ እና በሥርዓተ አምልኮው መካከል ያለውን ርቀት የሚያሰፋ እና የሚያነብር ነው ። ከላይ እንዳነሣሁት የአእላፋት ዝማሬ ከቤተ ክርስቲያን ርቆ የሚኖረውን በማማለል የመጥራት ብቻ ሳይሆን በማኅሌትና በቅዳሴ ይሳተፉ የነበሩትንም ሰዎች የማስሸፈት ውጤት ነው የነበረው ። የአእላፋት ዝማሬ አዘጋጆችም ሆኑ ሌሎች ሰዎች ዝማሬዎችና ስብከቶች ወደ ሥርዓተ አምልኮው የሚያደርሱ መንገዶች እንጂ ሥርዓተ አምልኮውን የሚጋርዱ ጽላሎቶች አይደሉም ማለታቸው ለምን እውነት እንዳልሆነም ቀደም ብዬ አሳይቻለሁ ። ለዓውደ ምሕረት ጉባኤ ሲባል ቅዳሴ ሳይነጋ የሚጀመርበትና የሚካለብበት ፥ ለአእላፋት ዝማሬ ሲባል ማኅሌት በለኖሳስ የተደረገበት ሀገር ላይ እንዲህ ማለት ቀልድ ነው ።

የራቁትን ለማቅረብ ፣ የጠፉትን ለመመለስ ፣ የሌሉትንም ለመጥራት ብቸኛው መንገድ ሥርዓተ አምልኮውን ወደ ማዕከልነቱ መመለስ ነው ። ይህን ስናደርግ ሥርዓተ አምልኮው ራሱ ልንኖረው የሚገባንን የክርስትና ሕይወት በዝርዝር ያስረዳናል ። ሕይወታችንን ከሥርዓተ አምልኮው ትእዛዝ ጋር ማሥመር ቀላል አይሆንም ። ብዙ ውጣ ውረድ ፥ ብዙ ድካም ይፈልጋል ። ብዙ ጊዜ ሊፈጅም ይችላል ። አማራጭ የለንም ፤ የተጠራነው ወደዚህ ሕይወት ነው ። ሥርዓተ አምልኮውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማዕከል ፥ የትምህርታችንም ዐቢይ ምንጭ ካደረግነው ከቤተ ክርስቲያን የራቁትን ለመጥራት ሌላ አማራጭ ፥ የደመቀ እና “ደረጃውን የጠበቀ” ሁነት ማዘጋጀት አይጠበቅብንም ። ሥርዓተ አምልኮው ራሱ ከማንም በላይ ጠሪ ነው ፤ ከምንም በላይ ውብ ነው ።

፨ ፨ ፨

[6] “And they who are well to do, and willing, give what each thinks fit; and what is collected is deposited with the president, who succours the orphans and widows and those who, through sickness or any other cause, are in want, and those who are in bonds and the strangers sojourning among us, and in a word takes care of all who are in need.”Justin Martyr, *First Apology*, Translated by Marcus Dods and George Reith (Roman Roads Media, 2015), Chapter 67 (p. 45)